# ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ

## የማህበራዊ ሳይንስ እና ስነሰብ ኮሌጅ

## የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

## “ፍቅር እስከ መቃብር ረጅም ልቦለድ ወደ ፍቅር እስከ መቃብር ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማ ከማላመድ ጽንሰ ሀሳብ አንጻር ትንተና”


በ

ሄኖክ መልካሙ



ሚያዚያ 2017 ዓ/ም

ወልቂጤ ዩኒቨርሲቲ ፤ ጉብሬ

የማህበራዊ ሳይንስ እና ስነሰብ ኮሌጅ

የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል

# "ፍቅር እስከ መቃብር ረጅም ልቦለድ ወደ ፍቅር እስከ መቃብር ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማ ከማላመድ ጽንሰ ሀሳብ አንጻር ትንተና"

በ

ሄኖክ መልካሙ

የጥናቱ አማካሪ

ረ/ፕ ወርቁ ሙሉነህ

## የአማካሪው ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ፅሁፍ በወልቂጤ ዩኒቨርስቲ የቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል የመጀመሪያ ድግሪ ማሟያ መስፈርት መሰረት ድጋፍ የተደረገለት መሆኑን አረጋግጣለሁ።

የአማካሪው ስም___________________________

ፊርማ_________________________________

ቀን___________________________________

ይህ ጥናት በ ሄኖክ መልካሙ ፍቅር እስከ መቃብር ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማ ከማላመድ ጽንሰ ሀሳብ አንጻር ትንተና በሚል ርዕስ የሰራዉን የመጀመሪያ ድግሪ ሟሟያ ፅሁፍ የዩኒቨርስቲውን ጥራት እና ደረጃ ያሟላ ለቴአትር ጥበባት ትምህርት ክፍል ተቀባይነት መሆኑን ማረጋገጫ ነው።

ይህም በፈታኝ ኮሚቴ ተረጋግጧል።

ፈታኝ አንድ

ስም__________________________

ፊርማ________________________

ቀን__________________________

ፈታኝ ሁለት

ስም___________________________

ፊርማ__________________________

ቀን___________________________

# ምስጋና

በመጀመሪያ ያለሱ ዋጋ የለም እና ለልዑል እግዚአብሄር ምስጋናው ከፍ ይበልልኝ በመቀጠል እዚህ ደረጃ እንድደርስ ከፍተኛ ሚና ለተጫወቱት ለቤተሰቦቼ እንዲሁም ይህን ጥናታዊ ጽሁፍ በምሰራ ወቅት ከጎኔ በመሆን ድጋፉ ላልተለየኝ አማካሪዬ ረ/ፕ ወርቁ ሙሉነህ በተጨማሪም ደግሞ የዚህች ዐለም ዛቢያ አዙራ እዚህ ዩኒቨርሲቲ ላገናኘችኝ ጓደኞቼ፤ በግቢ ቆይታዬ ከጎኔ በመሆን አስተዋጾ ላደረጉልኝ በመጨረሻም ለሄኖክ አስተዋጾ አድርጌያለው ብለው ለሚያስቡ ማንኛዉም ሰው ዋጋችሁ አፍርቷል። ፈጣሪ ከፍ ያድርግልኝ ለማለት እወዳለሁ!!

# አበርክቶ

ሄኖክ ይሄን ጠንካራ ማንነት እንዲገነባ ምክን ያት የሆነች የሷን ልጅነት በኔ ውስጥ ላሳደገች ከኔ ጋር ተዋህዳ አዚህ ደረጃ ላደረሰኝ ለተከበረችው ውዷ እናቴ እንዲሁም ለፍቶ ጥሮ ይሄን ከመሰለ ማንነት ትልቅ ደረጃ ለደረሰው እኔነቴ፤

የ ተ በ ረ ከ ተ

# አጠቃሎ

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ  ፍቅር እስከ መቃብር ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማ ከማላመድ ጽንሰ ሀሳብ አንጻር መጽሀፉን እንዴት ወደ ድራማ አመጡት የሚለዉን ይዳስሳል የጥናታዊው ጽሁፍም የተሰራው ገላጭ በተሰኘው የምርምር ዘዴ ሲሆን መጽሀፉን ደግሞ ደጋግሞ ድራማውን በአስተውሎ በመመልከት የተተነተነ ነው፤የተላመደው ስራም በትንተናው  አንድ አሸጋጋሪ ከልቦለድ ወደ ፊልም በሚያሸጋግርበት ወቅት የሚከተላቸው የተለያዩ ስልቶች ሲኖሩ በዋነኝነት ግን ስነ ጽሁፋዊ ይዘቱን መጨመር እና መቀነስ፤ቃላትን ወደ ምስል መለወጥ እና መቼቱን ወደ ፊልም መቼት መለወጥ ናቸው፡፡ ይህ ጥናት ከነዚህ ስልቶች አንጻር ፍቅር እስከ መቃብር ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማ ከማላመድ ጽንሰ ሀሳብ አንጻር  በሂደቱ ወቅት ጥሩ ያስባሉትን ለዋናው ስራ መታመኑን የሚያሳምኑ ምልከታዎችን በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ላይ ሰፍረው ይገኛሉ።

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምስጋና........................................................................................................I

አበርክቶ........................................................................................................II

አጠቃሎ........................................................................................................III

ማውጫ........................................................................................................IV

ምዕራፍ አንድ........................................................................................................1

መግቢያ........................................................................................................1

1.1 የጥናቱ ዳራ........................................................................................................3

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት........................................................................................................2

1.3 የጥናቱ ዐላማ........................................................................................................2

1.3.1 የጥናቱ ዓብይ አላማ ........................................................................................................3

1.3.2 የጥናቱ ንዑስ አላማ........................................................................................................3

1.4 ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች ........................................................................................................4

1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ........................................................................................................4

1.6 የጥናቱ ወሰን ........................................................................................................4

1.7 የጥናቱ ዘዴ ........................................................................................................4

1.8 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ........................................................................................................5

1.9 የጥናቱ አወቃቀር ........................................................................................................5

ምዕራፍ ሁለት ........................................................................................................6

የተዛማጅ ጥናታዊ ጽሁፍ........................................................................................................6

2.1 የፊልም ምንነት........................................................................................................6

2.2 የፊልም ጽሁፍ ምንነት........................................................................................................6

2.3 የልቦለድ ምንነት.........................................................................................................7

2.3.1 አጭር ልቦለድ..........................................................................................................8

2.3.2 ረጅም ልቦለድ..........................................................................................................8

2.4 የፊልም እና የልቦለድ ልዩነት ..........................................................................................9

2.4.1 ምስላዊ እና ቃላዊ.......................................................................................................9

2.4.2 ውስጠኛው ክፍል እና ውጨኛው ገጽ..............................................................................9

2.4.3 ድምጽ እና ዝምታ ....................................................................................................10

2.5 የቴሌቪዥን ድራማ ምንነት ...........................................................................................10

2.6 የማላመድ ምንነት ......................................................................................................11

2.6.1 ለቀዳሚው ስራ የታመነ ...............................................................................................11

2.6.2 ቀዳሚውን ስራ እንደመነሻ ብቻ የሚጠቀም.....................................................................11

2.7 የማላመድ ስልቶች .......................................................................................................12

2.7.1 ቃላትን ወደ ምስል መለወጥ .......................................................................................12

2.7.2 የስነጽሁፍ ይዘቱን መጨመር እና መቀነስ.........................................................................12

2.7.3 መቼት ወደ ፊልም መቼት መለወጥ.................................................................................13

2.8 በማላመድ ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮች.............................................................................13

2.8.1 የዕይታ አንጻር በስነጽሁፍ እና በሲኒማ.............................................................................14

2.8.1.1 አንደኛ መደብ የትረካ አንጻር ተግዳሮቶች....................................................................14

2.8.1.2 የሶስተኛ መደብ የትረካ አንጻር ተግዳሮቶች...................................................................14

2.8.1.3 የዕይታ አመራረጥ.....................................................................................................15

2.8.2 የርዝማኔና የጥልቀት ችግር...........................................................................................15

2.8.3 ፍልስፍናን ማንጸባረቅ...................................................................................................16

2.8.4 ቃለ ንግግር መረጣ.....................................................................................................16

2.8.5 የተደራሲው ስሜት.......................................................................................................17

ምዕራፍ ሶስት..........................................................................................................................18

መረጃ ትንተና..................................................................................................................18

3.1 የፍቅር እስከ መቃብር ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማ በአጭሩ/በ4ቱ ክፍል/...............................18

3.2 የማላመድ ስልት ምልከታ........................................................................................................19

3.3 በማላመድ ወቅት የተስተዋሉ ለውጦች..................................................................................19

3.3.1 ቃላትን ወደ ምስል መለወጥ..........................................................................................19

3.3.2 የጽሁፍ ይዘቱን ከመጨመር እና ከመቀነስ አንጻር .....................................................20

3.3.3 መቼትን ወደ ድራማ መቼት ከመለወጥ አንጻር.........................................................21

3.3.4 ታሪኩ ከዋናው ታሪኩ ጋር ያለው ተዕማኒነት............................................................22

3.3.4.1 በገጸባህርያት ዙሪያ...............................................................................22

3.3.4.2 በጭብጥ ዙሪያ.......................................................................................23

3.4 በማላመድ ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮች...............................................................................24

3.4.1 የትረካ አንጻር...........................................................................24

3.4.1.1 የአተራረክ ቅርጽ .............................................................................24

3.4.1.2 የዕይታ አመራረጥ .........................................................................24

3.4.2 የተደራሲው ስሜት.........................................................................25

3.4.3 ፍልስፍናን ከማንጸባረቅ..........................................................................26

3.4.4 የገጸባህርያት አሳሳል...............................................................................26

3.5 ቃለ ንግግር መረጣ....................................................................................27

ምዕራፍ አራት.........................................................................28

ማጠቃለያ...............................................................................28

ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው.......................................................................29

ዋቢ መጽሀፍት........................................................................................30

# ምዕራፍ አንድ

## 1.1 መግቢያ

ጥበብ ከሰው ልጅ አፈጣጠር ጀምሮ ስንመለከት እስከ አሁን የደረሰበትን ደረጃ አጀብ የሚያስብል ነው። የሰው ልጅ የኮራጅነቱ ባህሪው በአይነቱ እየተለየ እየሰፋ በመጣ ጊዜ የተለያዩ መሳሪያዎችን መጠቀም ጀመረ። የሰው ልጅ የኮራጅነቱን ባህሪውን ማንጸባረቂያው መሳሪያ ከሆኑት መካከል ፡- ልቦለድ፤ፊልም፤ስዕል፤እንዲሁም የመሳሰሉት ናቸው።ከመሳሪያዎቹ መካከል አንዱ የሆነውን ልቦለድን እንዳስስ፤ ልቦለድ የሚታይ፤የሚሰማ ነገር ነገር የሌለው በቃላት የተሰደረ ሲነበብ ለውስጠታችን ከሚታይ እና ከሚሰማ በላይ የሆነ ምስል ከሳች የሆነ ጽሁፍ በሀገራችን ከምንመለከታቸው ፊልሞች በተጨማሪ ተወዳጅነትን ያተረፉ የተለያዩ የልቦለድ ጽሁፎች ወደ ምስሉ የፊልም እንዱስትሪ ጋር ብናላምደው ተወዳጅ የሆኑስራዎችን ማቅረብ እንችላለን።"የፊልም ድርሰት አጻጻፍ ብልሀት" በሚለው የአዲስ ተስፋ መጽሀፍ እንዲህ ሰፍሯል፤

> *የኪነጥበባት ዘርፎች ማለትም ስነስእል፤ ስነጽሁፍ፣ ሙዚቃና ቴአትር የአንድን አገር ርእዮተ ዓለም እንዲወክሉ ሆነው በምናባዊ የፈጠራ ከሂሎች ተቀምረው ይቀርባሉ፡፡ ከነዚህ የኪነ ጥበባትዘውጎች መካከል ለዚህ መጽሃፍ የመጻፉ ሰበብ ስለሆነው የፊልም ጽሁፍ ምንነትእና እንዴትነት በዝርዝር ሳናወጋ ሊዘመዳቸው ስለሚችልባቸው ዘርፎች ማውሳቱ የግድ ይላል፤ ከባዶየሚጀመር ነገር የለምና፡፡ የፊልም ጽሁፍ ከፈጠራ ድርሰቶች ለምሳሌ ከረዥምና አጭር ልብወለድ፣ ተውኔት፣ ድራማ፣ ግጥም፣ ወጎችና ተዛማጅ የፈጠራ ስራዎች አንድ የሚያደርገው ባህርይ አለው፡፡ይኸውም የአንድን አገር፣ ወይም ዘመን ፍልስፍናዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ማኅበረ -ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊናፖለቲካዊ አመለካከቶችና አስተሳሰቦችን ጠብቆ ከትውልድ ትውልድ፣ ከዘመን ዘመን ያሸጋግራልና፡፡ እነህ ልዩ ልዩ ዘርፎች የየአገራቱን ማኅበረባህላዊ የእድገት ደረጃ ዎች ወስነውና መዝነው የማስቀመጥ ሚናቸው ከፍተኛ ነው፡፡ /1፤2003/*

በሀገራችን የልቦለድ መጽሀፍ ብለን ስንጠራ አብሮ የሚመጣልን ከሌሎች ባሻገር ፍቅር እስከ መቃብር የተሰኘው የክቡር ዶ/ር ሀዲስ አለማየሁ ረጅም ልቦለድ እናገኘዋለን።መጽሀፉ ምንም እንኳን በወጣ ሰሞን የአንባቢ እጦት ቢጋረጥበትም ኋላ ላይ ግን ወጋየሁ ንጋቱ ልቦለዱን ሲተርከው መጽሀፉ እጅግ ተወዳጅ እና ከዘመን ዘመን የማይደበዝዝን ዉበት ይዞልን ቆየ። አሁን ላይ ደግሞ ልቦለዱ ወደ ተከታታይ የቴለቪዥን ድራማ የመጣበት መንገድ የመጽሀፉን ተደናቂነት፤ተደራሽነት መስፋት ያሳየናል።

ለፊልም አዘጋቾቻችንም በሀገራችን የተለያዩ ተወዳጅ ፊልሞች እንዲሁም ተከታታይ ውስን ድራማዎችን እያስመለከቱን ነው'ድራማዎቹንም ከዚህ የበለጠ የተመልካች ቁጥር እንዲኖረው የተለያዩ ተወዳጅ የሆኑ የልቦለድ ጽሁፎችን ወደ ምስሉ ቢያላምዱ ኢንዱስትሪውን ከፍ ወዳለ ደረጃ የሚያደርሰው ይሆናል።

ለአንዳንዶቹ ጥበብ አፍ ሁና የማ/ሰቡን ችግር እይታ ፍላጎት መግለጽ ካልቻለ ምኑን ጥበብ ሆነ የሚሉም አይጠፉም ጥበብን ግን ከአፍ በተለየ እጅ እና አዕምሮ ችግሩን ከመናገር ወደ ችግር ፈቺነት መምጣት ካልቻለች ጥበብነቷን ያደበዝዝባታል።

## 1.1 **<u>የጥናቱ ዳራ</u>**

በሀገራችን በማላመድ ዙሪያ ለሚሰሩ ፊልሞች ከየት ተነስተው እስከ የት ድረስ መሄድ እንዳለባቸው የተለያዩ ድክመቶችን ቀድመው ተመልክተው ለጥንቃቄ ያህል እንዲያግዛቸው እና በሀገራችን በልቦለድ ጽሁፍ እና በፊልም መካከል ያለውን ቁርኝነት ከፍ ለማድረግ በተጨማሪምየፊልም ኢንዱስትሪውን በጥሩ ታሪኮች ታግዞ ላቅ ወዳለ ደረጃ ለማድረስ ነው ።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኚው የተለያዩ ተወዳጅ የሆኑ የልቦለድ ታሪኮችን ወደ ፊልም በማለመድ ለመስራት ስለሚፈልግ ፤
አጥኚው የፍቅር እስከ መቃብር ልቦለድ ሲያነብ መጽሀፉን ስለወደደው ፤ ወደ ተከታታይ ድራማ በሚቀየርበት ሂደት ውስጥ ሊፈጠሩ የሚችሉ ድክመቶችንንም ጥሩ ጎኖንች ገምግሞ ለማዉጣት ፤

## 1.3 የጥናቱ አላማ

### 1.3.1 የጥናቱ ዓብይ አላማ

የፍቅር እስከ መቃብር ረጅም ልቦለድን ወደ ፍቅር እስከ መቃብር የቴሌቪዝን ተከታታይ ድራማ ከማላመድ ጽንሰ ሀሳን አንጻር ትንትኔ መስጠት ነው።

### 1.3.2 የጥናቱ ንዑስ አላማ

የማላመድ ጽንሰ ሀሳብ ምንነት ማሳየት ፤

የልቦለድ ምንነትን ማሳየት፤ የፊልም ምንነት ፤ እንዲሁም የቴሌቪዥን ድራማ ምንነት ማሳየት፤

በተለያዩ ኢጋዝ መጽሀፎች እንዲሁም በማላመድ ጽንሰ ሀሳብ ዙሪያ በተሰጡ ሀሳቦች ፤ በመመርኮዝ የድራማዉን ጥንካሬውን እና ድክመቱን በመመልከት ትንታኔ መስጠት፤

## 1.4 ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች

የማላመድ ጽንሰ ሀሳብ ምንነት ምን ይመስላል ?

የልቦለድ ጽሁፎችን ወደ ፊልም ጽሁፍነት የመቀየሪያ መንገዶች ምን ምን ናቸው ?

በተከታታዩ ድራማ እና በልቦለድ ጽሁፉ መካከል ያለ መሰረታዊ ልዩነት እና አንድነት ምንድን ነው ?

ከልቦለድ አላባውያን አንዱ በሆነው ገጸ ባህርይ ፤ በተከታታዩ ድራማ ዉስጥ ገጸባህርያቶች እንዴት ተስለዋል ?

በልቦለድ አላባዉያን ውስጥ የሚጠቀሱትን ዝርዝር ነገሮች በተለይ ወሳኝ የሆኑትን አላባዉያን በተከታታዩ ድራማ ዉስጥ እንዴት ይገልጻል ?

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

ስለ ልቦለድን ወደ ፊልም ማላመድ ጽንሰ ሀሳብ ግንዛቤ መስጠት እንዲሁም በዚህ ሀሳብ ዙሪያ መስራት ለሚፈልጉ ጸሀፊያን ለሚሰሩት ስራ እንደ መነሻ ለማገዝ እና ሊኖሩ የሚችሉ ድክመቶች እና ጥንካሬዎች በድክመቶች ዙሪያ የመፍትሄ ሀሳብ በማስቀመጥ መመርኮዣ መሆን ፤

ለተለያዩ አንባብያን ስለ ማላመድ ጽንሰ ሀሳብ እውቀቱ እንዲኖራቸው ያግዛል

ፍቅር እስከ መቃብርን በመጽሀፍ ብቻ ለሚያውኩት የተከታታይ ድራማውን በሚመለከቱ

ጊዜ ሊፈጠረባቸው የሚችለውን ውዝንብር ሙያዊ በሆነ መንገድ ብዥታውን ለማጥራት

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ በክቡር ዶ/ር ሀዲስ አለማየሁ የተጻፈዉን ፍቅር እስከ መቃብር የተሰኘዉን ረጅምልቦለድ በሰውመሆን ይስማው ተዘጋጅቶ የሚቀርበዉን ፍቅር እስከ መቃብር ተከታታይ የቴሊቪዥን ድራማ በአምስቱ ክፍል ከማላመድ ጽንጸ ሀሳብ አንጻር ትንታኔ መስጠት ላይ ብቻ የተወሰነ ነው።

## 1.7 የጥናቱ ዘዴ

አጥኚው ይህን ጥናት ሲሰራ ገላጭ የምርምር ስልትን መሰረት አድርጎ ሰርቷል። ገላጭ የምርምር ዘዴ ከስሙ እንደምረዳው በጥናቱ ወቅት የሚሰራዉን ጽሁፍ ዉስጥ ያለውን ችግር አንስቶ በዛ ዙሪያ ላይ ማብራሪ የሚሰጥ ነው። "መሰረታዊ የምርምር ዘዴዎች" በተሰኘው የአለም እሸቱ በተሰኘው መጽሃፍ ላይ ተገልጿል።"ገላጭ ጥንታዊ ፅሁፍ በሁለት ተለዋዋጮች መካከል የሚኖረውን? ተዛምዶ እያነፃፀረ የሚተነትን የጥናታዊ ፅሁፍ አይነት ነው" (2001፤148) አጥኚውም የክቡር ዶ/ር ሀዲስ አለማየሁ "ፍቅር እስከ መቃብር"መጽሀፍበጥልቀት በማንበብ እና በስውመሆን ይስማው የተዘጋጀዉን ተከታታይ ድራማ በአስተውሎ በመመልከት እንደ መረጃ ምንጭነት በማላመድ ጽንሰ ሀሳብ ዙሪያ የታተሙ መጽሀፍቶችን በማንበብ ከተገኙት ምንጮች ጋር በመመልከት በገላጭ በተሰኘዉን የምርምር ዘዴን ተከትሎ የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ ነው።

## 1.8 በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች እና መፍትሄ

አጥኝው የማሊመዴ ጽንሰ ሀሳብ ከሌቦሆዴ ወዮ ዴራማ በሚሰራበት ወቅት በዘሪያ ስሆማሊመዴ ጽንሰ ሀሳብ የተሰሩ አጋዥ ጽሁፎችን ማግኘት አሌቻሆም ነበር ይህም ቀግሞ በምዕራፍ ሁሆት ሊይ ዜርዜር ጉዲዩ ሊይ የተሆያዩ ጸሀፊዎች ያስቀመጡትን ምርኩዜ የሚሆን የታተመ መጽሀፍቶች ማግኘት አሌቻሆም ነበር፤እንዮ መፍትሄ የወሰዮው ባገኛቸው የተሆያዩ የሀገር ውጭ መጽሀፍቶች ስሆ ጽንሰ ሀሳቡ በመረዲት በሚያገኛቸው ጥቂት ሀገራዊ ጽሁፎች እያስፋፉ ሰርቶ አብቅቷሌ።

### 1.9 የጥናቱ አወቃቀር

የዜህ ጥናት አወቃቀር በ4 ምዕራፎች የተከፈለ ነው። በምዕራፍ አንድ መግቢያ ፤ የጥናቱ ዳራ ፤ የጥናቱ ዐላማ ፡ ጥናቱ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች ፤ የጥናቱ ጠቀሜታ ፤ የጥናቱ ወሰን ፤ የጥናቱ ዘዴ የሚሉትን ይገኛሉ እንዱሁም ደግሞ በምዕራፍ ሁለት ላይ ስለ ዋና ጉዳያችን የማላመድ ጽንሰ ሀሳብ ምንነት፤የማላመድ ስልቶች፤የፊልም ምንነት፤የልቦለድ ምንነት የፊልም እና የልቦለድ ልዩነት፤በተጨማሪም ደግሞ የቴሌቪዥን ድራማ ምንነት ይገኛል

በምዕራፍ ሶስት ደግሞ የመረጃ ትንተና ይገኛል በመጨረሻው ምዕራፍ አራትም የማጠቃለያ ሀሳብ፣ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋዎች እና ዋቢ መጽሀፍትን በውስጡ አካቶ ይገኛል።

## ምዕራፍ ሁለት

## የተዛማጅጽሁፍቅኝት

### 2.1 የፊልም ምንነት

የፊልም ምንነት ገብተን ከመዳሰሳችን በፊት አመጣጡን እንመልከት፤የፊልም ታሪካዊ አመጣጥ ጊዜው ወደ 18ኛው ክ/ዘመን መገባደጃ የጀመረ ሲሆን በጊዜ ሲታዩ ከነበሩት ተንቀሳቃሽ ማሎች እስከአሁን የደረሰበት ደረጃ ሊደርስ ቿሏል።በዘላለምተፈሪ"የፊልምትወናጥበብ"በሚለውመጽሀፍላይእንዲህሲልሰፍሯል፡-

> የፊልም ጥበብ በተንቀሳቃሽ ምስል አማካይነት ለተደራሲያን ታሪክ
>
> የሚነገርበት እና መልዕክት የሚተላለፍበት፤የሰው ልጅ ኪነ ጥበባዊ
>
> የተግባቦት መንገድ ነው።አብዛኛዉንጊዜ ታሪኩ የሚነገረውበድርጊት
>
> እና በምስል ስለሆነ የ ፊልም ጥበባዊ እይታዊ ጥበብ ነው ማለት
>
> እንችላለን።/18፤2010/

ፊልም ሲታይ ፍሰት ያለው ማራኪ፤ዉብ የሆነ መስሎ ይቅረብ እንጂ በዋነኛነት የፊልም ውስጣዊ ምንነት ማንነት የፎቶግራፎች ክምችት ነው። እነህ የፎቶግራፍ ክምችት በጋራ በመሆን አንደኛው ከአንደኛው በሚተላለፍ፤በሚሰበሰቡ ጊዜ ማራኪ የሆነ ተንቀሳቃሽ የሆነ ምስልን ይፈጥርልናል።
በጥቅሉ በስክሪን ላይ የሚቀርቡልን ምስሎች የፎቶግራፍ ክምችቶች ናቸው።በተለምዶ የሚሰሩበት የፎቶ ክምችት በአንድ ሰከንድ 24 ፎቶ ነው እንዲሁም ደግሞ ተመካሪ የሆነዉም በሰከንድ የ24 ፎቶ ክምችት ነው።እንደ የስራችን ሌሎችም ተስማሚ የሆኑ አማራጮች አሉን ማለትም፡-"25fps፤30fps፤60fps..."እንግዲህ ይህን ስንል በአንድ ሰከንድ ውስጥ የሚተላለፉ የፎቶዎችን ብዛት ነው፤ምስል ከሳች የሆነ ማራኪ ፊልም/ድራማ አመጣጡ የሚታይ ነገርየሚሰጠንበፎቶክምችትነው።

### 2.2የፊልም ጽሁፍ ምንነት

የፊልም ጽሁፍ ምንነት ስንል ፡- በምንቆይበት የአንድ ሰዐት ተኩል ሊሆንም ይችላል ሁለት ሰዐት የጊዜ ፍጆታ በዛች ሰዐት ውስጥ የተመልካቹንም ቀልብ ተቆጣጥሮ ተወዳጅነትን አትርፎ ከዘመንዘምን ለመሻገር በፊልሙ ዉስጥ የሚቀርብልን የሙሉው ፊልም ታሪክ ነው።"የስኬታማ የፊልም አሰራር ከመደበኛው ህግጋት ባሻገር"በሚለው የኤልያስ ጋሻው መጽሀፍ እንዲህ ይለናል፤

" በግጭቶች የተገነባ ወይም ግጭቶችን መሰረት ያደረገ ሴራ የግድ ሊሆን የሚገባ መሆኑ ነው።ግጭትም ለፊልም ታሪክ ወሳኝ የማዕዘን ድንጋይ ነው። አስገራሚ ወይም አስደማሚ "surprisse"እና ሴራ ባልተገመተ አቅጣጫ መታጠፍ "reversal" ሌሎች መሰረታዊ የፊልም አላባውያን ሲሆኑ በተለይ መደነቅ፤ጉጉት ልብ መስቀል ለመፍጠር ያገለግላሉ።አስገራሚ ድንገቴ ለሁሉም አይነት ፊልሞች ቁልፍ መሳሪያ ነው። /2፤2007/

ፊልሙን በፍላጎት ለማየት የተመልካችን ቀልብ ከሚገዛልን መካከል ዋነኛው የፊልሙ ድርሰቱ ታሪኩ ነው። ምንም እንኳን የሌሎች ቴክኒካል ቡድኖች ስብጥር እንዳለ ቢሆንም በዋነኝነት ግን ተመልካችን የድምጽ ግብዐቱ ማማር፤የአርትዖት መመቸት ብቻ ስለመሰጣቸው በሰዐቱ ሊሳቡ ይችሉ ይሆናል እንጂ ዘላቂነትን የሚያተረፍ'፤ከዘመንዘመን ቢሻገር የማይደበዝዝልን ዉበትን ሊያጎናጽፍልን የሚችለው ድርሰቱ ነው።" የፊልም ድርሰት አጻጻፍ ብልሀት" በሚለው የአዲስ ተስፋ መጽሀፍ፡-"የፊልም ጽሁፍ ልንጽፈው የምንፈልገዉና በህይወታችን የምንወደው እንዲለወጥ የምንፈልገዉና በህይወታችን የምንወደው እንዲለወጥ የምንፈልገው፤አልያም የመረጥነው ታሪክ የሌለ ነገር ግን እንዲኖር የምንፈልገው አንዳች ጉዳይ...ወ.ዘ.ተ. ሊሆን ይችላል። ይህም ሂደት የተለያዩ ሀሳቦችን በመፈለግ እና በማግኘት የምንመርጠዉን አንድ ሀሳብ ውስን በማድረግ ይጀምራል። /54፤2003/ የፊልሙን ጽሁፍ ለመጻፍ ሀሳብ ዋነኛው ነገር ነው!ሀሳብ ወይም ታሪኩን የሚኮርጀው ደግሞ ከገሀዱ ዐለም ነጸብራቅ ነው። መኮረጁ ብቻም ደግሞም ሳይሆን የቀረበበት መንገድ የተገለጸበት ቃላቶች በዋነኝነት የታሪኩን የጽሁፉን ተወዳጅጅነት ይደምቅለታል። በተቃራኒው ግን የተገለጸበት ፤ የተንጸባረቀበት መንገድ ቃላቶች ዋጋቢስ ከሆኑ ሁሉም ጸሃፊ /ሀሳብ አመንጭ/ በሚባል ደረጃ የሚኮረጀው ከተመሳሳይ ነገር ከገሀዱ ዐለም ስለሆነ የተለየ ነገር ይዘው ካልመጡ ወይ ደግሞ የተሻለ የራሳቸውን የምናብ ፈጠራ ይዘው መቅረብ ካልቻሉ ተወዳጅነትን ማትረፍ አይችሉም።

የፊልም ጽሁፍ ለመጻፍ የተለያዩ ምንጮችን እንደ ሀሳብ ማመንጫነት ሊጠቀሙ ይችላሉ። ከእነዚህም መካከል፡- የተለያዩ ክስተቶች፤ከማ/ሰቡ ቁሳዊ እና ህሊናዊ ሀብቶች፤ከፈጠራ ስራዎች፤ከታሪካዊ ሁነቶች ጸሀፊው ካሳለፈው ህይወት፤ካለው ምልከታ እንዲሁም የተለያዩ መንገዶችን በማምጫ መንገድ በመውሰድ መጻፍ ይቻላል።
ከላይ ለማየት እንደሞከርነው ከፈጠራ ስራዎች ስንል ከተለያዩ ልቦለዶች፤ግጥም፤ወግ፤መጣጥፎች በጥቅሉ ከታተሙ የፈጠራ ውጤቶች ወደ ምስል/ፊልም/ ሚዲየም በማሸጋገር ሊሰሩ የሚችሉበት ሂደት ነው።

## 2.3 የልቦለድ ምንነት

ልቦለድ በቀጥታ ወደ ትርጉሙ ከመሄዳችን በፊት ቃላቱን ነጣጥለን እንመልከተው።"ልብ"እና"ወለድ" የተሰኘዉን ደግሞ መውለድ፤ማውጣት፤መገላገል የተሰኘን ፍቺ እናገኛለን። የሁለቱን ውጤቶች አንድ ላይ ስናዋህዳቸው ቃሉ "ልቦለድ" ትርጉሙ ደግሞ ውስጣዊ ከዉስጥ የመነጨዉን ማውጣት፤መገላገል ዉስጣዊ ሀሳብ፤ምልከታችንን በቃላት ማዉጣት መግለጽ መቻል ማለት ነው።
የተለያዩ ጽሁፎችን፤ልቦለዶችን ለመጻፍ ሀሳብ ለማመንጨት የተለያዩ መንገዶችን መጠቀማችን አይቀሬ ነው። ይህም የሆነበት የሰው ልጅ በዙሪያው የተሰማዉን፤ የቃኘዉን፤የደረሰበትን በደል እንዲኡሁም የምናብ አቅሙን ያለመጠቀም ዝንባሌ ካለው ወደ ገሀዱ ዐለም የሚከናወኑ ሚተገበሩ ጉዳዩችን በመኮረጅ በጽሁፍ ያሰፍራል፤"በስነ ጽሁፍ መሰረታዉያን":-የዘሪሁን አስፋው መጽሀፍ እንዲህ ይሰኛል"ልቦለድ ማህበራዊ ህይወትን በስፋት በሚጥምና በሚስብ ዘይቤ የማሳየት አቅም ያለው፤የሰውን ልጅ አያሌ ገጠመኞች ማቅረብ የሚችል ኪነ ጥበባዊ ቅርጽ ነው። ከሌሎቹ የስነጽሁፍ ዘርፎች የበለጠ ዘላቂነት ያላቸው የተስፋፉና የበለጸጉ የሰዎች ምስሎችን የመያዝ አቅም አለው።በልቦለድ የሰው ልጅ

ሀዘንናደስታ፤ጥላቻናፍቅር፤ምኞትናፍላጎት፤ብልጽናናውድቀት፤በአጠቃላይ ግብሩና አተያዩ በኪነታዊ ዘዴ ይቀርባል። /145፤2005/ የኮረጀውን ነገር በጥበባዊ ቃላቶች ሰድሮና አዋህዶ በጽሁፍ መልክ ሲያቀርብልን ልቦለድ እንለዋለን። ልቦለድ ግን ከቃሉ ትርጉም አንጻር የሚያዋህድልን የጸሀፊውን ችሎታ አቅም የሚያሳይልን ንጹህ የሆነ የልብ፤የውስጣዊ ልጅ ሁኖ ሲወለድ ነው። በተጨማሪም የገሀዱን ዐለም ነጸብራቅ በሚገባ ቃኝቶ ተመልክቶ የውስጡን ፤የተሰማዉን እንዲሁም ሲከናወን የተመለከተውን ጥዑምም በሆኑ ቃላቶች ሰድሮ አንድን ሀሳብ ካንዱ፤አንዱን ሁኔታ ከሌላኛው አዋህዶ የሚጻፉ ጽሁፎችም ቢሆኑ የአንባቢያን ቀልብ መግዛት ይችላሉ።
ልቦለድ ካለው የቃላት ብዛት እንዲሁም የገጽ መጠን እና ረጅም እና አጭር ልቦለድ ተብለው በሁለት ይከፈላል።

## 2.3.1 አጭር ልቦለድ

አጭር ልቦለድ ማለት በልቦለዱ ውስጥ የተጠቀሰዉን ታሪክ ከሰውልጅ መሰረታዊ ሁነቶች ፖለቲካዎች፤ማህበረሰባዊ እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ የሚፈጠሩ ተግዳሮቶች ክስተቶች ተዋዝቶ ተዋህዶ የቀረበልን የልቦለዱ ታሪክ በቃላት ከ30000 ያነሰ ሲሆን አጭር ልቦለድ ብለን እንጠራዋለን። ዘሪሁን አስፋው "የስነ ጽሁፍ መሰረታውያን" በሚል ርዕስ ባሳተመው መጽሀፍ ስለአጭር ልቦለድ እንዲህ ይለናል"የሚተረከው ታሪክ ብዙ ሳይጠማዘዝ ቶሎ ቶሎ መተረክ አለበት፤ትልሙና የተለዩ ክፍሎች ፍሰታቸው ጠብቀው ዝርዝር ነገር ባያበዛ ፤ የተስፋፋ የመቼት ገለጻ ባይኖረውና ገጸባህርያት ሳይለጠጥ በፍጥነት መዳዝ አለባቸው።"/230፤2005/
በዚህ የልቦለድ አይነት የተለያዩ አላባውያኖች ውስን ሊሆኑ በቅጡ ሊመለከቱት አይችሉም በታሪኩም ዙሪያ ነጠላ የሆነ ሴራ የተሸከመ ሁኖ ልናገኘው እንችላለን።

## 2.3.2 ረጅም ልቦለድ

ረጅም ልቦለድ ስንል ደግሞ ልቦለዱ ከላይ ባየነው በቃላት በኩል 30ሺና ከዛ በላይ የሆነ የቃላት ክምችት ያለው በውስጡ የተገለጸው ታሪክ ሴራ፤ልል ነጠላ ያልሆነ ውስብስብ የሆነ ሴራ ያለው የማይረግጠው የማይገልጸው የሚቀረው ቦታ የሌለው በሁሉም አቅጣጫ እንደ ደራሲው የምናብ መሻት እየዞረ የሚዳስስ በአላባዉያኖችም እጅግ ሰፊ የሆነ ገለጻን ያለው የጽሁፍ አይነት ነው። ብርሀኑ ገ/ጻዲቅ "አጠቃላይ የአማረኛ ቋንቋ" በሚል ርዕስ ባሳተመው መጽሀፍ የረጅም ልቦለድ ብያኔ እንዲህ ይለናል"ረጅም ልቦለድ ሰፊና ውስብስብ ግጭቶች፤ረጅም ልቦለድ ብዙ ቅርንጫፍ ጭብጦች፤ብዛት ያላቸው ገጾች እና ከ80ሺ ባላነሱ ቃላት ይጻፋል።/46፤2008/
በሁለቱም የልቦለድ አይነቶች የተጋነነ ልዩነት ባይኖርም ሊፈጠሩ ከሚችሉት ልዩነት መካከል አጭር ልቦለድ የተለመደ የአተራረክ ቅርጽ እና ቅደም ተከተሉ ግልጽ የሆነ አጭር ሲሆን በረጅም ልቦለድ ጊዜ የተወሳሰበ ታሪክ ቅ/ተከተል ያለው እና እጅግ ሰፊ የሆነ የሰው ልጅ የህይወት ልምድ የሚዳስስ ይሆናል በጊዜ ፍጆታ በኩልም ረጅም ልቦለድ በታሪኩ ዉስጥ ያለው የጊዜ ቆይታ ብዙ ዓመታቶችን በውስጡ ሊይዝልን ይችላል። እንዲሁም መጽሀፉን ተደራሲያን ሲያነቡት ረጅም ጊዜ ሊፈጅባቸው ይችላል። በአጭር ልቦለድ ጊዜ ግን በውስጡ የሚጠቀሰው የጊዜም ቆይታ መጽሀፉንም ለማንበብ የሚወስደው ጊዜ እጅግ አጭር ነው።

## 2.4 የፊልም እና የልቦለድ ልዩነት

ፊልም እና ልቦለድ የተለያዩ የኪነጥበብ እልፍኞች እንደ መሆናቸው እንደ ተምሳሎታቸውም ልዩነት አላቸው። በዋነኛነት ልዩነቱ ላይ ትኩረት ሰጥተን የተመለከትንበት ምክንያት ሁለቱም የኪነጥበብ እልፍኞች እንደመሆናቸው ጥበብን እንደሚያንጸባርቁ ተምሳሌታቸው ላይ የተለየ ነገር ስለማይነሳ ነው።

### 2.4.1 ምስላዊ እና ቃላዊ

ሁለቱም የኪነጥበብ እልፍኞች የየራሳቸው የሆነ የታሪክ ንግርትን ይጠቀማሉ። ልቦለድ ታሪኩን ለመናገር ሀሳብ ምልከታውን በቃላት ሲያስተላልፍ ወደ ምስል ከሳቹ ፊልም ስንመጣ ደግሞ ሀሳብ ታሪኩን የሚገልጽ ምስልን በመወከል ነው። "ዘ ዲፈረንስ ቢቲዊን ኖቭልስ ኤንድ ፊልም ኢንሀንስ" በተሰኘው የባአ መጽሀፍ እንዲህ ተሰኝቷል"... በሁለት ነገሮች መካከል ያለዉን ግ ንኙነት ለማብራራት ምልክት እና ምስል ተጠቅሟል አንድ ነገር ሌላውን ሲወክል montgomery 1992,p.193/ ምልክቱ የሚያመልከተው በግብዐታዊነት ነውው በሁለት ነገሮች መካከል ያለው ግ ንኙነት ለምሳሌ፡- "አበባ" የሚለው ቃል የአበባ ምልክት ሊሆን ይችላል፤በተጨማሪም የአበባ ስዕል ሊሆን ይችላል፤ይህም በሁለቱም መካከል እምብዛም ግብታዊናዝምድና እንደሌለው ያሳያል። /59፤2008/" በፊልም ላይ ሁሉም ነገሮች በቃላት መግለጽ ያልተቻለውን በምስል መከሰት ይቻላል። ልቦለድ ላይ ግን ያለምንም ቃላት ልቦለድ እሙናዊነቱን ያጣል የፊልም ሜዲየም ነገሮችን በተንቀሳቃሽ ምስል ቁልጭ አድርጎ ሲያስቀምጥ በልቦለድ ደግሞ በምናብ ለማየት የሚያዳግቱ ግራ ሚያጋቡ ምናቦችን በቃላት ቁልጭ አድርጎ ማስቀመጥ ይችላል።

### 2.4.2 ውስጠኛው ክፍል እና ውጨኛው ገጽ

ውስጣዊ እና ውጫዊ ገጽታ ብሎ የገለጸው ፊልም በባህሪው ምስሉን በሚቀዳ ወቅት የአንድን ገጸ ባህሪ ውጫዊ ገጽታ የሚያደርገዉን እና በዙሪያው የሚከናወነውን ሁነቶች ብቻ ነው። "ዘ ዲፈረንስ ቢቲዊን ኖቭልስ ኤንድ ፊልም"ጽሁፍ ላይ እንደቀረበው እንዱህ ይሰኛል" ።" ይላል በውስጡ የሚፈጠሩትን የተለያየ የስሜት መለያየት የውስጥ ወግ ለማሳየት ሌላ አይነት ዘዴ መጠቀሙ የግድ ነው። በልቦለድ ላይ የገጸባህሪው የውጨኛው ምስለት በቃላት ከመገለጹም በላይ ውስጡ ላይ የሚመጡ ማንኛዉም ሀሳቦች ምልከታ የሀሳብ ምልልሶች በሚገባ በቃላት ይገልጽላቸዋል።ይህም በሁለት ሚደየም ላይ የሚፈጥረው ልዩነት ሁኖ እናገኘዋለን።

### 2.4.3 ድምጽ እና ዝምታ

"ዘ ዲፈረንስ ቢቲዊን ኖቭል ኤንድ ፊልም"" በሚለው “የፊልሙ ድምጽ የአድማጮችን ግ ንዛቤ በእጅጉ ሊያሻሻል እንደሚችል እሙን ነው። የፊልሙ ታዳሚዎች መረጃዉን ከምስልም ከሆነ ከድምጽ ማግኘት ሲቻል ልቦለድ አንባቢዎች ግ

ን ከጽሁፉ ብቻ ነው። ድምጹ በፊልሙ ውስጥ በ3 አይነት ማለትም በንግግር፤በሙዚቃናበድምጽ ሊመደብ ይችላል።" /59፤2008/

በድምጽ እና ዝምታ ላይ ፊልም ላይ በይበልጥ ተመልካች አድማጭ ላይ የድምጽ ግብዐቱን በማጥፋትም ይሁን እንደ ተገቢው ሁኔታ መግለጽ ሲችሉ ልቦለድ ላይ ግ ን ታሪኩ ሙሉ በሙሉ በቃል ፤ በጽሁፍ ስለሆነ የሚገለጽ ስልለሆነ ይገደባል።

በአጠቃላይ በፊልም እና በልቦለድ መካከል ያለ ልዩነት ፊልም ምስል ላይ ትኩረት ሲያደርግ ልቦለድ ግ ን ሙሉ በሙሉ በትረካ ላይ መሰረት ያደረገ ነው። ፊልም ላይ በማዋነኛነት ስሜቶችን በቀጥታ የመፍጠር አቅም ሲኖረው ልቦለድ ግ ን ስሜቶችን በተዘዋዋሪ ነው የሚፈጠሩ ም/ቱም በቃል  የተቀመጠ የተሰደረ ስለሆነ ከአንደኛው ወደ አንደኛው ለመሸጋገር የሚወስደው ቆይታ ተዘዋዋሪ ያደርግበታል። እንዲሁም በመጨረሻ ጠቅለል ስናደርገው ፊልም ላይ የምናየው ነገር ለአፍታ ብናቆም ብዙ ነገሮች የሚያልፈን ሲሆን ልቦለድ ላይ ግ ን ትኩረታችን ሙሉበሙሉ በቃላቶች በኩል ማለፉ የግዴታ ስለሆነ የሚያመጣልን ነገር አይኖርም።

## 2.5 የቴሌቭዥን ድራማ ምንነት

የቴሌቭዥን ድራማ ምንነት በአንድ የቤተሰብ ታሪክም ሆነ በሆነ ክስተት ሁኔታ ላይ ቅ/ተከተሉን በያዘ መልኩ በተሰደረ ጥሩ የሆነን የታሪክ ፍሰትን በውስጡ የያዘ ፤ የድራማ/የፊልም ወይም አንድ የጥበብ ስራን ሚሚላት ካለባቸው አላባዉያን ብዙሀኑ አላባውያኖችን የጋራ የሆነ ተምሳሎት ስላላቸው የቴሌቭዝን ድራማም ይህን መሰረት የሚሆነውን አላባውያን ያሟላ በምስል የሚቀርብልን የድራማ አይነት ነው። በዴቪድ ሰልፊ የ"ቴሌቪዝን ድራማ ኢንትሮዳክሽን" መጽሀፉ መግቢያው ላይ እንዲህ ሲል ይስተዋላል" በአንድ አይነት ልቦለድ ታሪክ ላይ የሚያጠነጥኑ ተከታታይ ሀሳቦችን ጥርቅም የያዘ  ድራማ ነው።"/2፤1984/ ይህም ማለት የተከታታይ ድራማ ውስን የሆነና ረጅም የሆነ ይዘት ያለው ድራማ እናገኛለን። ውስን ስንል የድራማው ይዘት አጭር በሆነ ጊዜ የሚጠናቀቅ ጭብጡ ሙሉበሙሉ ታሪኩ በአንድ ሁነት ላይ ዙሪያ ብቻ የሚያደርግ ሲሆን ሌላው ደግሞ ረጅም ያልነው በብዙ ምዕራፎች እና ክፍሎች የተዋቀረ ሴሪየስ ሁኖ ስናገኘው ነው። በእጸገነት እንዳለ ጥናታዊ ጽሁፍ ላይ እንደቀረበው"የምን ልታዘዝ የቴሊቪዥን ድራማ ከሳታየር ኮሜዲ ባህርያት አንጻር "ተከታታይ ታሪክ ድራማ ወይም ሴሪየስ ድራማ የምንለው የተወሳሰበ የትረካ ይዘት ያለው ሲሆን እነዚህ የተወሳሰቡ ሀሳቦች በየትዕይንቶች ውስጥ አንድን ሀሳብ በመያዝ ወይም በመደገፍ ሀሳብን በይበልጥ ያብራራል።/6፤2011/

## 2.6 የማላመድ ምንነት

የማላመድ ምንነት ማለት የሆነን ጥበባዊ ስራ ወደ ሌላ የጥበብ ስራ ማላመድ መቻል ማላእት ነው። "ዘ አርት ኦፍ አዳፕቴሽን" በተባለው የሴገር ሊንዳ መጽሀፍ ውስጥ የማላመድ ብያኔ በዚህ መንገድ ቀርቧል"ሽግግር ከአንድ የጽነጽሁፍ ዘርፍ ወደ ሌላኛው ዘርፍ ኪነጥበብ የመቀየር መንገድ ነው።"በተጨማሪም "የፊልም ጥበብ ቅኝት"በተሰኘው የወሰኘለህ ትርጉም መጽሀፍ እንደሚከተለው ቀርቧል"ማላመድ/ውርስ/በሌሎች ስራዎች ላይ ተመስርቶ የሚሰራ ፊልም ነው። በሆሊውድ ውስጥ ከሚሰሩት ፊልሞች መካከል የውርስ ስራዎች ድርሻ ቀላል አይደለም። ውርስ ስራ እያንዳንዱን ገጸ ባህርይ

እና ይዞት እንዳለ በታማኝነት ወደ ፊልም ከማምጣት ጀምሮ ብዙ ነገሮችን ጨምሮ እስከ መስራት ሰፊ ልዩነት ያለው ተግባር ነው።" /344፤2005/

የማላመድ ጽንሰ ሃሳብ በጥቅሉ አንድን የኪነጥበብ ስራ ወደ ሌላ የኪነጥበብ ስራ ማላመድ፤ማዋረስ፤መቀየር ማለት ነው።ይህ የኪነጥበብ ስራ ጽሁፍ ሊሆን ይችላል ተውኔት፤ግጥም፤ሙዚቃ ማንኛዉም የኪነጥበብ አይነት ወደሌላ ሜዲየም መቀየር ወደ ተቀየረው የጥበብ አይነት ማዋሀድ ማጣጣም መቻል ማለት ነው። አንድን ጥበባዊ ስራ በምናሸጋግርበት ወቅት ለተሸጋገረበት ሜዲየም የማይመጥን የሚረብሽ ነገር ሊኖረው አይገባም፤እንዲሁም ደግሞ ለእናት ስራው ማሟላት ያለበት ሊከተለው የሚገባ ሁለት አይነት የማላመድ መስፈርቶች አሉ።ማለትም አንድን የኪነጥበብ ስራ በሚላመድበት ወቅት ስራው ከሁለቱ አንደኛዉን ተከትሎ በዛ መሰረት የተላመደ ስራ ነው የሚያቀርብልን ማለት ነው።

### 2.6.1 ለቀዳሚው ስራ የታመነ

የመጀመሪያው ዋናው ኪነጥበባዊው ስራወደ ሌላኛው የጥበብ እልፍኝ በምናሻግርበት ወቅት የተለመደው ስራ ለመጀመሪያው ስራ የታመነ እና ከመጀመሪያው ከያዘው ሀሳብ ማፈንገጥ መቻል የለበትም። በብሩክ መንግስ ጥናታዊ ጽሁፍ ላይ እንዲህ ሲል ገልጾታል "ይህ የመጀመሪያው ጽንፍ አንድ የልቦለድ ስራ ወደ ፊልም በሚለወጥበት ጊዜ ለቀዳሚው ስራ ተዐማኒ በመሆን በልቦለዱ ያለን ሃሳብ ወይንም ፍልስፍናን በማይለውጥ መልኩ መሸጋገር አለበት የሚል ሀሳብን የያዘ ነው።"

### 2.6.2 ቀዳሚውን ስራ እንደ መነሻ ብቻ የሚጠቀም

ይሄኛው መንገድ ደግሞ የሚያተኩረው የሚነሳልን ሀሳብ ወይም የሚላመደው ጽሁፍ ልክ ከላይ ባየነው መልኩ በእናት ስራው ስር መዋል ሳይኖርበት የመነሻ ሀሳቡን ወይንም ማስተላለፍ የፈለገዉን ነገር መርጦ በማዉጣት ወደ ሚቀየረው የጥበብ ስራ ተስማሚ እና አመቺ በሆነ መንገድ ለተደራሲያን ማቅረብ ነው።ይሄኛው መንገድ ለሚያላምደው አካል ነጻነትን ያውጃል ምክን ያቱም በ መጀመሪያው በኩል ስር ላይ የግዴታ ሳይቆይ ሀሳቡን መነሻዉን ብቻ በመውሰድ የራሱን የሆነ ፈጠራ በማከል የተመቸዉን ስራ እንዲሰራ ያስችለዋል።

## 2.7 የማላመድ ስልቶች

በማላመድ ስልቶች በብሩክ መንግስት ጥናታዊ ጽሁፍ ላይ የተጠቀሱትን 3 የጽንፍ አርዕስት በመውሰድ እንዳስሣለን።

### 2.7.1 ቃላትን ወደ ምስል ማላመድ

ከላይ ቀደም ሲል ለማየት እንደሞከርነው በሁለቱም ሚዲየም ያሉትን ልዩነት ቃላትናምስል ተጥቃሽ ነበሩ። በልቦለድ ዉስጥ መናገር፤ማስገንዘብ፤ማመልከት የፈለጉትን ነገር በቃላት/በጽሁፍ ላይ ብቻ መግለጽ የሚችሉ በዚህ ጊዜ ደግሞ አንድ ልቦለድ

ወደ ድራማ በምናላምድበት ጊዜ ቃላቶቹን ወደ ምስል መከሰት ግዴታችን ነው። በባአ "ዘ ዲፈረንስ ቢቲዊን ኖቭል ኤንድ ፊልምስ" በሚለው መጽሀፍ እንዲህ ሰፍሯል
"ከመግለጽ አቅም አንጻር ፊልም የሚገነባው በምስል ነው።መጽሀፍ ደግሞ በጽሁፍ፤ በዚህም የተነሳ የፊልም ምስሎች ሊገልጽ ከተፈለገው መልዕክት ጋር ቀጥተኛናተከታታይነት ያለው ግ ንኙነት/ቁርኝነት/ይኖራቸዋል።በተጨማሪም በፊልም ላይ ያለ የድምጽ ግብዐት ተመልካቹን በከፍተኛ ሁኔታ መልዕክቱን እንዲረዳው ይረዳዋል ስለዚህ ፊልም ለእውነታው የቀረበ ተጨባጭ ስሜትን ይሰጣል በሌላ በኩል የፊልም ይህ አይነቱ ባህሪ ከልቦለድ በተሻለ በቀላሉ እንድነረዳው ያስችለናል።/58̈ ፤59፤2008/
በዚህ ጊዜ እንግዲህ ልቦለድ ላይ የአንባቢን ቀልብ ለመስቀል በተለያዩ የቃላት ገለጻ ፤ የቃላት አሰዳደር ተጠቅሞ ሁኔታዉን ሊገልጽ ሲችል ወደ ፊልም በሚዘዋወር ጊዜ ግ ን የቀረበውን ሀሳብ ደቂቃ ባልሞላ ሁኔታ ውስጥ በምስል ሊከስትልን ይችላል። ልቦለድ ላይ በልቦለዱ ውስጥ የተገለጹትን ገጸባህርያት ያላቸውን ሚና፤ሀላፊነት፤ግ ንኙነት ላማሳየት እልፍ ገጾችን እና ቃላትን ሊጠቀምይችላል ወደ ፊልም መልስ ስንል ግ ን ያንን ያህል የፈጀን ሁኔታ በጥቂት ደቂቃዎች የስሜት መሸራረፍ፤መጓደል ሳይኖር ቅልብጭ አድርጎ ሊያሳይ ይችላል።

## 2.7.2 የስነጽሁፍ ይዘቱን መጨመር እና መቀነስ

ልቦለድ ወይንም አንድን ጽሁፍ ወደ ድራማ በምናላምድበት ጊዜ ሙሉበሙሉ የልቦለድ ጽሁፉ ቃልበቃል ይቀየራል ብሎ ማለት የማይመስል ነገር ነው። በ"የፊልም ጥበብ ቅኝት" የወሰን የለህ መጽሀፍ እንዲህ ይሰኛል"የአንድን ተወዳጅ መጽሀፍ ወይም ቴአትር ውርስ ፊልም ስንመለከት መጽሀፉን ስናነብ ወይም ቴአትሩን ስናይ የነበረውን ነገር ፊልሙ እንዳለ ገልብጦ የሚያቀርብልን አድርገን ልናስብ እንችችላለን፤ነገር ግን ያ የሚሆን አይደለም።" /344፤2005/
ምክንያቱም ደግሞ የየሁለቱ የጥበብ ጓዳ የተላያየ አይነትን የየራሳቸው የሆነ መለያ ያላቸው ስለሆነ ስለዚህ ደግሞ አንድን ጥበባዊ ስራ ወደ ሊአላኛው ወይንም ልቦለድን ወደ ድራማ በምናላምድበት ወቅት በልቦለዱ የተገለጹ ቃላቶች እንደየአስፈላጊነቱ ይጨመራሉ ይቀነሳሉ። ልብ ሊባል የሚገባው ግ ን የሚያላምደው አካል እንደሚከተለው ዘዴ ማለትም ለእናት ስራው መታመን አለበት በሚለው ከሆነ የምንቀንሰዉም የሚጨመረው ታሪክ ከዋናው ስራ የተጣጣመ የማይቃረን የተዋሀደ መሆን መቻል አለበት ።
ይህ የሆነበት ምክኛት እንደ ምሳሌ የሚላመደው ስራ አጭር ልቦለድ ወደ ፊልም/ድራማ ቢሆን አጭር ልቦለድ በባህሪው በውስጡ ያሉት ገጸባህርያት የተሳሉበት መንገድ ሚናቸው በስርዕቱ የተገለጸ ሁኖ ላናገኘው እንችላለን በዚህ ጊዜም ከ እነርሱ ጋር የሚሄድ ሀሳብ እና ማንነትን ጨምረንላቸው ወደ ፊልሙ/ድራማው ልናመጣቸው እንችላለን።በተዘዋዋሪም ረጅም ልብለድን ወደ ድራማ በምናላምድበት ወቅት ጥሩ የሆነን ነጻነትን ሊቸረን ይችላል ይህን ስንል ወደ ተከታታይ ድራማ አሻገርነው ነው ማለት ድራማው ውስን ካልሆነ በውስጡ ብዙ ምዕራፎች እና ክፍሎችን የተጎናጸፈ ስለሆነ የልቦለዱን ሀሳብ ከእርዝማኔ አንጻር በመስጋት መቀነስ አስፈላጊ ሁኖ ላይመጣብን ይችላል ስለዚህ ትኩረታችን የሚሆነው ሀሳቡ ወደ ምስል በሚጣጥታም መልኩ ማላመዱ ላይ እንድናተኩር ጊዜ ይሰጠናል።

## 2.7.3 መቼትን ወደ ፊልም መቼት መለወጥ

የድራማ መቼት በጽሁፍ ላይ የቀረበለትን ግልጽ የሆነ ቦታ ከገሀዱ ተስማሚ የሆነዉን መርጦ በምስል ያስተዋውቃል። በልቦለዱ ጊዜ ላይ ግ ን ደራሲው ገጸባህርያቶቹ ነእሮችን በሙሉ የሚከናወኑበትን፤የተለያዩ የግዳጅ ስራዎችን የሚፈጽሙበትን ቦታ በስራ ቦታቸው የሚፈጠርባቸዉን ደባሪ ሁኔታ ና የመሳሰሉትን ለተደራሲያን ለማድረስ በተለያዩ ቃልቶች አጣጥመው ለንባብ ማብቃት መቻል አለባቸው። በብሩክ መንግስት ጥናታዊ ጽሁፍ ላይ "አልፎ አልፎ ልቦለዶች ባዛት ያላቸውን ትዕይንቶች ይዘው ይገኛሉ በዚህ ጊዜ አሸጋጋሪው ከትዕይንቶቹ መካከል ከታሪኩ ሀሳብ ጋር የሚሄዱና አይቀሬ የሚላቸውንመምረጥ ይኖርባቸዋል...።"ይህም የተሻለናላቅ ያለ ቦታ እንዲኖረው ያስችለዋል፤ቢሆንም ግ ን ልቦለዱን አሻጋሪው የልቦለዱን መቼት ወደ ድራማ መቼት በሚቀየርበት ጊዜ በልቦለዱ ውስጥ ያሉትን ገጸ ባህሪ በመቼ ዘመን እና በየትኛው ቦታ የሚለዉን ነገር ከግምት ማስገባት ምቻል አለበት ። ምክንያቱም የልቦለድ ጸሃፊው ስንት መቶ ቃላቶችን ሰድሮ የሁኔታውን ድባብ በዚህ ቤት ይገልጽልኛል ያለዉን ነገር በተቀመጠለት ብቻ ያስቀምጠዋል ማለት አደለም በጊዜው በዘመኑ ምን ይመስላል? የተሰኘዉን ነገር ከኘት ማስገባት መቻል አለበት ።እንዲሁም በዚህ ጊዜ ልቦለድ በባህሪው እጅግ በጣም ትዕይንቶችን በውስጡ ጠቅሶ ስለሚያሳልፍ የሚያላምደው አካል ከተንዛዙ ትዕይንቶች በመጭመቅ አሳጥሮ በአንድ በሁለት ቦታዎች ሊገልጽላቸው ይችላል። እንዲሁም ደግሞ በልቦለዱ ውስጥ በምናብ፤በሃሳብ ያሉትን በቃላት ለመግለጽ ምቹ የሆኑትንም ወደ ድራማ መቼት ሲመጣ አዲስ መቼትን ፈጥሮ ሊያሳይ ይገባል።

## 2.8 በማላመድት ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮች

አንድን ኪነጥበባዊ ስራ ወደ ሌላ የጥበብ እልፍኝ በምናላምድበት ወቅት ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮች እንደሚኖሩ እርግጥ ነው ም/ቱም በመጀመሪያው ወቅት ላይ የለመዱትን ስራ ወደ ሌላ ሜዲየም ሲመጣ የተደራሲያን ምልከታ ሊወዛገን ስለሚችል"የፊልም ጥበብ ቅኘት" በሚለው የወሰን የለህ መጽሀፍ.

"የአንድን ተወዳጅ መጽሀፍ ወይም ቴአትር ውርስ ፊልም ስንመለከት መጽሀፉን ስናነብ ወይም ቴአትሩን ስናይ የነበረውን ነገር ፊልሙ እንዳለ ገልብጦ የሚያቀርብልናድርገን ልናስብ እንችላለን፤ነገን ግ ን ያ የሚሆን አይደለም የምናውቃቸውን ስራዎች ውርስ ፊልም ስንመለከት ልክ የምንወደው ጓደኞችን ተለይቶ ቆይቶከዓመታት በኋላ ተለውጦ ስናገኘው የሚሰማንን ዓይነት ስሜት ሊፈጠር ይችላል።ከነዚያ ዐመታት በኋላ አዕምሯችን ያረጀ ሰው ጠብቆ ሆኖም እንግዳ ነገር ቢገጥመን ያ ሰው ለውጦችን እና በምንጠብቀው ልክየማድረግ ስልጣኑ እንደሊለው ብናውቅም መደንገጣችን አይቀርም።አንድን ስራ ወደ ስክሪን ስናመጣው የሚፈጠረው ለውጥ ልክ በዕድሜ ም/ት እንደሚፈጠረው አይቀሬ ነው። /344፤2012/

## 2.8.1 የዕይታ አንጻር በስነጽሁፍ እና በሲኒማ

"የፊልም ጥበብ ቅኘት"በተሰኘው የወሰን የለህ መጽሀፍ"በስነጽሁፍ የዕይታ አንጻር የሚገልጸው ደራሲው ድርጊቱን እና ታሪኩን በቀረበበት ምቹ ሁኔታ ነው። በፊልም "የዕይታ አንጻር የሚለው ጽንሰ ሃሳብ በጥቅሉ ገጸባህሪው ከሚያርፍነት ቦታ ጋር ተያይዞ የሚደረኘ ቀረጻ ይመለከታል።በሌላ በኩልም አጠቃላይ ታሪኩ እንዴት ቀረበ የሚለውን ለማሳየትም ይውላል።ልቦለድን ወደ ፊልም ለመቀየር የሚያስብ የፊልም ሰሪ የልቦለዱን የዕይታ አንጻር ወደ የፊልም የዕይታ አንጻር እንዴት መቀየር እንዳለበት አስቀድሞ መወሰን ይኖርበታል ስለዚህ ከስነጽሁፍ የዕይታ አንጻሮች ጋር መወሰን ይኖርበታል።

ስለዚህ ከስነጽሁፍ የዕይታ አንጽሮች ጋር መተዋወቅ ጠቃሚ ነው።፤/በወሰን የለህ ጥላሁን 347 348 2012/ ወሰን የለህ በስራው ትርጉም ስራ ላይ ይህን ይህን ካስጨበጥዕን በኋላ የዕይታ አንጻሮችን እንደሚከተለው አጥኝው ይዳሣል።

## 2.8.1.1 አንደኛ መደብ የትረካ አንጻር ተግዳሮቶች

አንደኛ መደብ የትረካ አንጻር የታሪኩ ባለቤት በልቦለድ አካል በሚተርከበት ወቅት እኔ እያለ የሚናገርበት ነው። ብዙሀኑ ምሁራኖችም ይህን የትረካ ስልት የጀማሪዎች ነው በማለት ይሰይሙታል “የፊልም ጥበብ ቅኝት በተሰኘው የወሰን የለህ መጽሀፍ እንዲህ ተገልጿል።”አንደኛ መድብ የትረካ አንጻር ትክክለኛ የሆነ ሲኒማዊ አቻ የለዉም በአንድ የድርጊት ተሳታፊ ዕይታ አንጻር የሚቀርጸዉን ካሜራ ወይም subject camera/ ሙሉ በሙሉ ሳይቋረጥ ጥቅም ላይ በማዋሉ ቴክኒክ በፊልሙ ውስጥ ውጤታማ አይደለ።ውጤታማ መሆን ችሎ እንኳን ቢሆን በስነጽሁፍ ውስጥ ላለው አንደኛ መደብ ትረካ አንጻር ትክክለኛ አቻ ተደርጎ ሊወሰደ አይችልም። “/350፤2012/

## 2.8.1.2 የሶስተኛ መደብ አንጻር ተግዳሮቶች

ይሄኛው የትረካ መደብ ተራኪው በልቦለዱ ውስጥ ያሉትን ማንኛዉም የገጸባህርያት ውስጣዊ ፤ውጭዊ ፤ ሀሳብ ሙሉበሙሉ የሚያውቅ የሚደረገውን የሚያይ ከአንዱ ሁኔታ ወደ አንዱ እየተዘዋወረ መተረክ የሚችል ነው። በ”የፊልም ጥበብ ቅኝት” የወሰን የለህ መጽሀፍ እንደተገልለጸው “ሁሉን አወቅ፤ውስን ሁሉን አወቅ ፤ ግለወግ የዕይታ አንጻሮች የትኛውንም የገጸባህሪውን ሀሳብ  ወይም የገጸባህውን ምላሽ ማየት እና መግለጽ ይችላሉ።ይህ ለሲኒማ አዳጋች ነው። ለእንደዚህ አይነት ችግሮች የተዘወተረው መፍትሄ የልቦልለዱን የዕይታ አንጻርና ሀሳብ ላይ ያለዉን ትኩረት ወደ ጎን በመተው ድራማዊ የሆኑትን ትዕይንቶች መቅዳት ነው።” /349 እና350፤2012/

## *2.8.1.3 የዕይታ አመራረጥ*

አንድን ጥበባዊ ስራ ወደ ሌላ የጥበብ ስራ ስንቀይር በተለይ ደሞ መጽሀፍን ወደ ምስል በምናመጣበት ወቅት የመጽሀፉን ዕይታ ቀድሞውኑ ልብ ብሎ ተረድቶ የጽሁፉን መሰረት ሳይለቅ ለምስል ተስማሚ በሆነ መንገድ መቅረብ መቻል አለበት። በዕይታ አመራረጥ ላይ ከግምት ልናስገባው የሚገባ ነገር ሰዎቹ ምን ይመስላሉ? የት ነው ያሉት? ምን ውስጥ ነው? ጊዜው መቼ ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች በአተኩሮ በማስተዋል መመለስ መቻል አለበት እንግዲህ ከላይ ያሉትን ጥያቄዎች እንደ አስረጅነት ሁለቱን ጠቅሰን እንመልከታቸው፤ሰዎቹ ምን ይመስላሉ? ይህን ጥያቄ በምናነሳ ወቅት መልሳችን ሊሆን የሚገባው ቀይ፣ጥቁር፣አጭር፣ረጅም ከሚሉት ምላሽ ባሻገር፤ ምን ይመስላሉ? ሁኔታቸው እንዴት ነው ከዘመኑ ጋር ምን አይነት ገጽታ ይፈጥርባቸዋል፣ምን አይነት አልባስ ይጠቀማሉ፣የተለያዩ ክንውኖችን ከማ/ሰቡ ጋር ሲከውኑ ምን ይጠቀማሉ በድርጊታቸው ጊዜስ ምን ይመስላሉ…የተሰኙትን እና ሌሎችንም በማገናዘብ መሆን አለበት፤በተጨማሪም ጊዜው መቼ ነው? ስንል ደግሞ ጊዜው በ90ዎቹ መገባደጃ አለቀ! ማለት መልስ ሊሆን አይችልም በጊዜው ዉስጥ አብረው የተዋሀዱ ዘመኑን የሚከስትልን

የተለያዩ ነገሮችን ልብ ልንል ይገባል በጊዜ ዉስጥ የጊዜው የአነጋገር ዘይቤ አለ፤የዘመኑ አረማመድ አለ፤የዘመኑ ቁሳቁሶች አሉ እንዲሁም ጥቃቃን የሚመስሉ ነገር ግ ን ዘመኑን የሚደምቁልን ነገሮች ልብ ብለን ማስተዋል መቻል አለብን።
በጥቅሉ በዕይታ መረጣ ላይ አዘጋጁ ይገልጽልኛል ያለዉን የቦታ የአልባስ እንዲሁም የራሱን የሲኒማቶግራፊ ዕይታ ከታሪኩ ጋር በሚዋሀድ በሚገልጽ መልኩ አድርጎ ማቅረብ መቻል አለበት ።

## 2.8.2 የርዝማኔናየጥልቀት ችግር

አንድን ልቦለድ በተለይ ደግሞ ረጅም ልቦለድን ወደ ፊልም በምናላምድበት ጊዜ  የርዝመቱ ነገር አሣሳቢ ነው ምክን ያቱም ፊልም በተገደበለት የ2ሰዐት ቆይታ ዉስጥ ረጅሙ ልቦለድ ከአንዱ ወገን ወድሌላኛው በጥልቀት በነጻነት የዳሰሰውን ቦታ ፊልም ላይ ስንቀይር የርዝማኔው ነገር ችግር ይሆናል ፤በተዘዋዋሪ ድራማ ከሆነ ግ ን መጠነኛ የሚባል ነጻነት ሊሰጠው ይችላል በተለይ ለረጅም ልቦለድ ተስማሚ የሚሆነው ወደ ተከታታይ ድራም ቢቀየር ነው ም/ቱም ተከታታይ ድራማ በብዙ ክፍሎች የተሰባጠረ ስለሆነ ከረጅም ልቦለድ ጽሁፍ ጋር አይቃረነዉም በወሰን የለህ "የፊልም ጥበብ ቅኝት" መጽሀፍ ላይ እንዲህ ሰፍሯል
“ፊልም ካለበት የጊዜና በአግባቡ ሊጠቀምባቸው ከሚችላቸው ቁሳቁሶች ስፋት ውስንነት የተነሳ ረጅም ልቦለድ በጣም በጥልቀት ያነጻቸውን ነገሮችን በስዕል ዳሶ ለማለፍ ይገደዳል ።የልቦለድ እና የፊልም ድርሰት ጸሀፊው ዊልየም ጎልድ መን ይህንን ችግር ጠቅለል አድርጎገልጾታል"ሰዎች' ልክ እንደ መጽሀፍ ነው?'ብለው ሲጠይቁ ምላሹ 'መጽሀፉን ፈጽሞ የሚመስል ፊልም በዐላማችን ታሪክ ጨርሶ ሊኖር አይችልም።'ነው"በጣም ተሳካ ቢባል ፊልሙ ሊያካክተው የሚችለው የረጅም ልቦለዱን ጥልቀት አነስተኛ ክፋይ ብቻ በመሆኑ ነው።ፊልም ሰሪዎች ቀሪዉን ነገር በሆነ መንገድ ለማጸባረቅ መሞከር አለባቸው።” /352፤2012/

## 2.7.3 ፍልስፍናን ማንጸባረቅ

ፍልስፍናን ስንል ደራሲው የዋናውን ጽሁፍ ምልከታዉን አስተያየቱን ወደ ሚቀይርበት ሜዲየም ላይ አብረንማጓዝ መቻል አለብን። በፍልስፍናው ውስጥ መግለጽ ማስተላለፍ መናገር የፈልገዉን ነገርን በውስጡ ይካተታል።"የፊልም ጥበብ ቅኝት" በሚለው የወሰን የለህ መጽሀፍ እንዲህ ይሰኛል “በረጅም ልቦለድ ውስጥ ጎልተው ከሚታዩ ነገሮች መካከል አንዱ ጸሃፊው በሆኑ የህይዎት እውነታዎች ላይ ያለዉን አስተያይ የምናይበት እና የእኛም አዕምሮ በእነዚህ አስተሳሰቦች የሚጸረቅበት ሰፊ ዕድል መኖሩ ነው። እነዚህ ጉዳዮች በውጫዊ ድርጊት የሚገለጹ ሳይሆኑ ካሜራ ሊደርስበት የማይችለውን የዐለም ክፍል የአንባቢውን አዕምሮ ለዛ ባለው ምርምር እያስጓዙ ውስጣዊ ጥያቄዎችን የሚያጭሩ ናቸው።” /353፤354፤2012/
 እንዲሁም በብሩክ መንግስት ጥናታዊ ጽሁፍ እንዳነሳው"....ይህም ልቦለድ ከስፋቱ እና ደራሲው የፈቀዳቸውን የቃላይ አደራድ ተጠቅሞ በምናቡ በፈለገው መንገድ ሃሳቡን ማስጓዝ፤የመፈላሰፍ የመጠየቅ እንዲሁም የመዳሰስ ነጻነትን ሲኖረው እነዚህ ነገሮች ወደ ፊልም ገልብጦ ለማምጣት አዳጋች ሆነው ሲገኙ በፊልሙ ውስጥ ላይካተቱም ይችላሉ።”
በደራሲው ዕይታ ውስጥ ስንሆን ከታሪኩ ጋር እንገናኛለን ጸሀፊው ሀሳቡን የገለጸበት መልዕክቱን ያንጸባረቀበት ታሪኩ ሳይጓደል መቅረብ መቻል አለበት ። ታሪኩ በሚቀየር ወቅት ለዋናው ስራ አመኔታውን በተላመደው ስራ ላይ ግልጽነቱን ማስቀመጥ መቻል አለበት።  ለዋናው ስራ ሲታመን ገጸ ባህርያትን፤ዋናው መልዕክት ጭብጡን ከግምት ማስገባት አስፈላጊ

ነው ከእነዚህ አንጻር ግ ን ሲሆን መልዕክቱ ከዋናው ጋር የተጓዘ ነው ወይስ አደለም? ብለን ስንጠይቅ መልሱን እናገኛለን በገጸባርያትም በኩል ቢሆን ሁኔታቸው የእናት ስራውን ዳና እየተከተለ ነው ውይስ አደለም ለምን ተቀነሰ እንዴት ተጨመረ ሚለውንም ማንሳት የግድ ነው ማለት ነው።

## 2.7.4 ቃለ ንግግር መረጣ

በሁለቱ የተለያየ ሜዲየም የሚጠቀሙት የቃላት አይነት እንደ የባህሪያቸው የተለያየ መንገድ መጠቀማቸው አይቀሬ ነው።አንድ ለንባብ የሚቀርብን ጽሁፍ ለምስል እንደሚቀርብ የጽሁፍ አይነት አመሳስሎ ማስቀመጥ የጽሁፉን ዋጋ ዝቅ ያደርግበታል ለንባብ የሚበቃ ማንኛዉም ጽሁፍ ዘወትር ከተለመዱት የቃላት አይነቶች ለይት ብሎ መገኘቱ የጽሁፉን ዋጋ ዉዴታ እንዲጨምር ያስችለዋል፤እንዲሁም ደግሞ ምስል ላይ የቀርቡ ማንኛዉም ነገሮች የግዴታ በቃል ተብለው ማለፍ አለባቸው ማለት አይደለም ም/ቱም በምስል ጊዜ የራሱን የሆነ ጽሁፉን ይገልጽልኛል ያለዉን ውክልና በዙሪያው ካሉት ነገሮች አጣምሮ ስለሚያቀርብልን በተጨማሪም በካሜራ ዕይታ የሚቀርቡልን እና በጽሁፍ የቀረበን ጽሁፍ የቃላት ዋጋቸው አንድን ነው ማለት አንችልም የምስሉ ላይ በተለምዶ በዕለትተዕለት የምንጠቀመዉን ንግግር መጠቀም ሲያስችለን በልቦለድ ወይም ጽሁፍ ላይ ግን ከዕለትተዕለቱ ወጣ ብሎ ቃላቱ ጠጠር ማለት መቻል አለበት ።

## 2.7.4 የተደራሲው ስሜት

ተደራሲው በመጽሀፍ አንባቢያን በፊልሙ ተመልካች የማናቸዉንም የጥበብ ታዳሚያን ተደራሲ እንላቸዋለን። እኝህ ተደራሲያን የቀረበላቸውን የለውጥ ስራ ሲያዩት ቀድሞዉንም የተቀያሪው ማለትም የፊልም ተመልካች ከሆኑ ውዴታ አድናቆትን ነገርግን መጽሀፉን ያነበቡ ከሆኑ ቅሬታን ሊፈጥር ይችላል ይህም የሚሆንበት ም/ት በልቦለዱ ውስጥ ይሉትን ገጸ ባህርያት ተደራሲው ባከው የምናባዊ እይታ ነጻነት እንደፈለገ አድርጎ የራሱን የሆነን የተሟላ ገጸባህሪ በውስጡ ስለሚስልንና ያ የሳለው ገጸባህሪ ወደ እይታው / ፊልም ሲቀየር ካሰበው ጋር ዝቅ ወይም ከፍ ሊልበት ስለሚችል ነው።በብሩክ መንግስቱ ጥናታዊ ጽሁፍ ላይ
በሽግግር ወቅት ላሽጋጋሪ አስቸጋሪ ከሚሆኑት ነገሮች አንዱ የተሳሉትን ገጸባህርያት ሊተኩ የሚችሉ ተዋኛን አግኝቶ በአካል ማቅረብ ነው።ይህም ማለት በተለያዩ የመጸሀፍት ተደራሲያ ምናብ ዉስጥ የተሳሉትን ገጸባህርያት ወደ አይነት ሁኔታ መመለስ አስቸጋሪ ስለሚሆን ነው።......የሽግግር ስልትን ተከትሎ በተሰራ ፊልም ላይ ሂስ ለመስጠት መጽሀፉን ከማንበብ ይልቅ በቅድሚያ ፊልሙን መመልከትእንድደሚሻል ምሁራን ይስማሙበታል ም/ቱን ሲያስቀምጡ በመጀመሪያ መጽሀፉን ያነበበ ሰው በምናብ የሚፈጥረው ምስል ስለሚኖረው ከራሱ ሃሳብ ጋር እያነጻጸረ ትክክለኛ ፍርድ መስጠት ስለሚያስቸግረው ነው ይላሉ።
እንዲሁም ደግሞ የሚያላምደው አካል የተደራሲያንን ቅቡልነት እንዲጎናጸፍ ስራው ተደራሲውን ከግምት ማስገባት መቻል አለበት ። ተደራሲው ደግሞ የተላመደው ስራ ከዋናው ስራ ወጣ ያለ የማይዋሀድ እንዲሁም በስራው ላይ የቀረቡት አካላት በተጋነነ ሁኔታ የእናት ስራው ላይመስሉ ከቻሉ ካልሆነ በስተቀር ስርዕት ባለው ሁኔታ ሁሉንም ባገናዘበ የቀረበ ከሆነ ቅቡልነታቸው ጥሩ የሚባል የማይሆንበት ምንም ም/ት የለም።

# ምዕራፍ ሶስት

## የመረጃ ትንተና

### 3.1 የፍቅር እስከ መቃብር ተከታታይ ድራማ በአጭሩ/በ4ቱ ክፍል/

*በጎጃም ዙሪያ ማንኩሳ በምትባል አውራጃ የሚኖሩ ቦጋለ መብራቱ እና እመት ውድነሽ  የተባሉ የሁለት ዐለምሰዎች ነበሩ፤ቦጋለ በድህነት አድጎ በድህነት ያለፈ ጎልማሳ ሲሆን ውድነሽ በጣሙ ደግሞ በባላባት ቤተሰቦች የተወለደች ለትዳር ስትደርስ ግ ንጓባሎች አግብታ የሞቱባት በዚህም ም/ት ከቤተሰቦቿ ተለይታ የኑሮዋን ውጣ ውረድ በም/ሰቡ ከሚደርስባት የሽሙጥ ክፍያ ጋር ትቻችላ ኑሮዋን የምትገፋ ሴት ነበረች ።*
*እነህ ሁለቱ ጥንዶች በቦጋለ ፍላጎት እና በውድነሽ ነፍስ አባት አማልጅ ተጋብተው በዛብህ የተሰኘ ልጅ ወለዱ።በዛብህ ገና በልጅነት ዕድሜው ላይ ቤተሰቦቹ ሊቋቋሙት ያልቻሉት በሽታ ስለተጋረጠበት እናቱ በልመና ይሄ ቀረሽ ለማይባል ታቦት ልጇን ቃል ትገባለች ።በዚህ ሀሳቧ ባለቤቷ ቅር ቢሰኝም ከመቀበል በቀር ምርጫ ስላልነበረው እያንገራገረም ቢሆን ልጃቸው ተሽሎት ይዘልቃሉ፤በየመሀሉም የቃልኪዳኑን ወረታ በገንዘብ ከፍለን ነጻ ይሁን ቢላትም ልጇን የምታጣው እየእመሰላት አሻፈረኝ ትላለጭ የኋላ ኋላ ላይ ግ ን ልጃቸው ከፍ እያለ እያደገ በቤ/ን አገልግሎቱ ደምዎዝ ክፍያ ማግኘት ሲጀምር እና ቤተሰቦቹን መደጎም ሲጀምር አገልጋይ ሁኖ በመቀጠሉ ደስተኛ ይሆናሉ፤የአባቱ የዘውትር ጭንቀት ግ ን በማምሻየ ጊዜየ ላይ ብደክም ደጋፊ መርኩዝ የሚሆን ልጅ አለኝ ለልጄ ግ ን በደከመ ጊዜ ደጋፊ ምርኩዝ የሚሆነውንልጅ ተድላ አለመታደሉን ሲያስታውስ ቅር ይሰኛል።*
*በዛብህ ከፍ ብሎ ሲጎመራ በርሱ ላይ የደረሰበትን ነገር ሲያውቅ ሊሸሸው ይፈልጋል፤ለዚህም ይሻለኛል ብሎ የወሰነው ከቤተሰቦቹ ርቆ መለየትን ነበር እንደሻተውም ከቤተሰቦቹ ኮብልሎ ዋሸራ፤ዙራምባ፤የተሰኙት ሀገራት ላይ የዕውቀት አድማሱን እያሰፋ ደብረወርቅ ላይም ውዴታን አትርፎ መማሩን ይቀጥላል።*
*ቤተሰኖቹም በውሳኔውስጣቸው ቢጎዳም መቀየር የሚችሉት ሁኔታ ስላልነበር አሜን ብለው መቀበልን መርጠዋል፤እመት ውድነሽ ግ ን ዘወትር ማማረር፤ማላዘን የዘወትር ስራዋ ስለነበር አይኖቿ ታውረዋል፤ቦጋለ ግ ን ሁሌም ቢሆን ማማረር ይቅርብሽ ባይሆን ፈጣሪን መማጸኑ ነው የሚበጀን ነበር የዘወትር ምክሩ እሷ ግ ን ከዚህ የባሰ ም ን ሊመጣብን እያለች ምሬቷን ተያይዛዋለች ኑሯቸውም ከቀንቀን መደፍረስ ጀምሯል።*
*በዛብህ ባረፈበት ደብረወርቅ ዙሪያ አቅራቢያ ፊታውራሪ መሸሻ የተባሉ መኮነን እና ው/ሮ ጥሩይነት  ሰብለ የምትባል ልጅ ወልደው ይኖራሉ።ሰብለ ወንጌል የቱንም ያህል ውብ ብትሆን ባል የማግቢያ ጊዜዋ እየመሸባት ነበር ውብት ከቁምነገር ሳያንሳት በቤተሰቦቿ ወግ አጥባቂነት ም/ት ልጃችን የተከበረ ካላገባት ቁማቀር ብትሆን መልካም ነው በማለት አቁመዋት ቀሩ እርሷም ብትሆን የዘወትር ምሬቷ በቤተሰቦቿ ክብር ም/ት ሁሌም እንዳማረረች ነበር።*
*በዛብህ ለት/ት ያረፈበት ዲማ የተሰኘ ቦታ በነበረው ቆይታ ባቀረበው ስራ ሑሉም በርሱ ድንቅ ችሎታ ተደንቀው የደብሩ አለቃ ቀጣይ ላለው ትልቅ ክብረበዕል እንዲመራ ያጩታል .........*

## 3.2 የማላመድ ስልት ምልከታ

በፍቅር እስከ መቃብር ረጅም ልቦለድ የሚያላምደው አካል የተጠቀመው ለዋናው ስራ መታመን የተሰኘውውን ጽንፍ ነው። ም/ቱም በድራማው ላይ የተገለጹት ማንኛውም ክስተቶች በመጽሀፉ ዉስጥ የተገለጸና እንዲሁም ያጠናከረ ለመጸሀፉ ዉበትን የሰጠ ነው.ይህም ማለታችን በመጽሀፉ ውስጥ የተገለጹት በሀሳብ ፤ብንግግር በአፍ ማነብነብ የተረፉትን ሀሳቦች በድራማው ላይ ወለል ብለው ነፍስ ዘርተው ሲቀርቡ ይስተዋላሉ።

በተጨማሪም ለዋናው ስራ የታመነ ስልት የተከተለ ስራ ሆነ ማለት ለእናት ጽሁፉ የታመነ የሆነ እና ለሚቀየርበት ሜዲየም ተስማሚ በሆነ መልኩ መቀነስ መጨመር ያለበትን የጸሀፊዉን ፍልስፍናን በማይነካ መልኩ የማከልም ዪሁን የመቀነስ ሙብቱ የተጠበቀ እንደሆነ ይታወቃል። ስራዉም ይህንን ከታሳቢነት በማስገባት ጥንቃቄ የተሞላበት ለዋናው ስራ ተዐማኒነት ያለው በጣም ጥሩ ስራ ነው ላማለት ያስችለናል።

## 3.3 በማላመድ ወቅት የተስተዋሉ ለውጦች

### 3.3.1ቃላትን ወደ ምስል ማላመድ

ቃላትን ወይም ደግሞ ጽሁፍን ወደ ምስለ ዕይታ መለወጥ ላይ ሀሳቡን በሁለት መልኩ እንመለክከተዋለን።

ይህን ስንልም ምንማለታችን ነው?....በልቦለድ ጽሁፍ ሀሳቦች በዋናነት በሁለት መልኩ ለአንባቢያን ይፈሳሉ፤ማለትም የልቦለዱ ባለቤት ገጽ ባህርይው ከሌላም  ገጸባህርይ ጋርም ሆነ ከሌሎች ጋር በሚኖረው የቃላት ልውውጥ ጊዜ ላይ እና ጸሀፊው በተጨማሪ አንባቢያን የጽሁፉ አካል የሆኑ ያህል እንዲሰማቸው ስሜትን የሚፈጥርበት የትርክት ወይም ደግሞ የታሪክ ነገራ ሁኔታዎችን የሚገለጽበትን ጽሁፍ ለማት ነው።

በድራማው ላይ አንድ ገጸ ባህሪ ለሌላይኛው ገጸ ባህርይ በቃል ተግባብቶ ለአንባቢ የሚፈጥረውን ምስል ማለትም በጽሁፍ ጊዜ በምስል የተገለጸበት ሁኔታም እጅግ በጣም አሪፍ ነው ለአስረጅነት ያህል፡

በመጽሀፉ ላይ እመት ውድነሽ በጣሙ  ከነፍስአባቷ ባል እንድታገባ አማላጅነት ለምነዋት ተስማምተው  ከወጡ በኋላ የሚቀጥለው ክንውን በገጽ 18 በምዕራፍ 1 ላይ

*“ እመት፡ ውድነሽ ፡ ፊታቸው ፡ ትንሽ ፡ እን ደማዘን ፡ ብሎ = እመስታዋ·ቱ፡ ፡ ውስጥ ፡ ያለችው፡ ከብ ፡ ፊትም ፡ እሳቸው ፡ ሲያዝኑ ፡ አይታ ፡ እንደማዘን ፡ አለች ። ግንባራቸ ውን ቁጥር ' አይናቸውን ፡ ትኩር ፡ አድርገው ' በተመለከ ቱዋት ፡ መጠን ፡ አዝና ፤ ግንባርዋ ፡ ከቅንድቦችዋ ፡ መሀከል ፡ ታጥፎ ፤ ከዚያ ፡ በላይ ፡ ከፍ ፡ ብሎ ፡ ስድብ ፡ በጉልህ ፡ ተጽፎ ' አዩ ፤ አነበቡት፡ “አንቺ፡ ባሎችሽን ፡ የፈጀሽ ፡ የባል፡በሽታ፡” ይላል ፡ ስድቡ ። "የማንኩላው ; አባቴ ; የማንኩሳው ፡ አባቴ ፡ ምነው ፡ ምን ፡ አልሁህና ፡ ስድብ ፡ ላማረው ፡ ሁሉ ፡ መስደ ቢያ አደረግኸኝ ፡ እባክህ ' በቃሽ ፡ በለኝ !” አሉና ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ መስታዋቱን ፡ ጥለው ፤ አይናቸውን ፡ በሁለት ፡ እጃ ቸው ፡ ሸፍነው ፡ ያለቅሱ ' ጀመር ። “*

ከላይ ያየነውን ገላጻ በድራማው ላይ በምዕራፍ አንድ ከመጽሀፉ ገለጻ ጋር አዋህዶ አመሳስሎ ራስኑ አድርጎ ያቀረበበት መንገድ ለተደራሲያን ምቹ ነበር። እንዲሁም በተጨማሪ በሌላኛው የጽሁፍ ገላጻ መልኩ ስንዳስስ ለአብነት ያህል በመጽሀፉ ላይቦጋለመብራቱን

*ጎጃም ' ዳሞት' አውራጃ ፡ ውስጥ ፡ ማንኩሳ ' በምትባል '*

*አገር ቦጋለ መብራቱ የሚባሉ ብዙ ዘመን በብቸኝነት*

*ነት ፡ የሚኖሩ ' ሰው ፡ ነበሩ ። ቦጋለ ፡ መብራቱ' ከድሀ ' ቤተ ' ሰብ ' የተወለዱ ' በዚያውም ፡ ላይ ፡ ድሆች ፡ ወላጆቻቸው ገና በሀጻንነታቸው ሞተውባቸው ድህነት ሲያንገላታ ' ቸው ' ያደጉ ፡ ነበሩ ። ትንሽ ' ከፍ ፡ እንዳሉ ፡ መጀመሪያ ፡ የፍ ዬልና ፡ የጥጃ ' እረኛነት ፡ እዬተቀጠሩ ፡ በሁዋላም ፡ እጃቸው ፡ እርፍ ' ለመጨበጥ ፡ ያክል ፡ መበርታት ፡ ሲጀምር ' ግብርና ፡ እዬተቀጠሩ ፡ ይኖሩ ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ሁኔታ ፡ እኩል ' እድሜያ ቸውን ' ካሳለፉና ፡ የምሽት ፡ ማግባት ፡ ፍላጎታቸው ፡ እየተ ቀነሰ ፡ ከሄደ ' በሁዋላ - በጉልማሳነታቸው ፡ ጉልበታም ' ወዲ ያው ' ጤናማ ፡ በመሆናቸው ' ረዳት ፡ ሳይፈልጉ ፡ ራሳቸውን ፡ ረድተው ፡ ለመኖር ፡ ቢችሉም ፡ ምሽት ፡ ካላገቡ ' እድሜያቸው ፡ ı እየገፋ ' እቅማቸው ፡ እየተቀነሰ ፡ ሲሄዱ ፡ ረዳት ፡ የሚያጡ ፡ መሆናቸውን ' ወዳጆቻቸው ' አጥብቀው ' ስለመከሩዋቸው ' "*

ከላይ የተገለጸውን ገላጻ በድራማው ላይ ያቀረበበት መንገድ የቦጋለን ብቸኝነት ያሳወቀበት መንገድ በስራው ወቅት ለስራው ያለውን ክብር ያሳየበት መንገድ በሌሎች ዘንድ ያለውን መስተጋብር በዋነኛነት በምዕራፍ 4 ı6ኛው ደቂቃ በምስል የተገጸበት መንገድ ጥሩ ዕይታ መሆኑን ይደመድምልናል። በመጨረሻም ጽሁፍን ወደ ምስል ከመለወጥ አንጻር በገጸ ባህርያት ከተባሉት ንግግርም ሆነ በልቦለዱ በዝርዎ ጽሁፍ ለገልጸ ከቀረቡት ወደ ምስል የተላመዱበት መንገድ ጥሩ ነው ለማለት ያስችለናል።

### 3.3.2 የጽሁፍ ይዘቱን ከመጨመር እና ከመቀነስ አንጻር

የጽሁፍ ይዘቱን ከመጨመርና ከመቀነስ አንጻር በድራማው ወቅት በልበ ሙሉነት ልንዳስስ ልናወራ የምንችለው በድራማው ላይ የተጨመሩትን በኩል ነው፤ም/ቱም ተከታታይ ድራማው ያልተቋጨ ስለሆነ በሌሎቹ ክፍል ላይ ተጠቅሰው ሊያልፉ ስለሚችሉ ቢሆንም ግ ን እስከ መጀመሪያዎቹ ካሉት ክፍሎች ግ ን የግድ መጠቀስ ያለባቸው የተቀነሱ ካሉ እንመልከታቸዋለን።

በጥቅሉ የጽሁፍ ይዘቱንበማላመድ ወቅት ሙሉበሙሉ ከማውጣት ከማስወገድ ይልቅ የድራማው ስራ ተመራጭ ያደረገው ተነግረው መተላለፍ ያለባቸውን ሀሳብ ከማስወጣት ወደ ሌላኛው ገጸባህርይ በማስተላለፍ ሳይገልጽ እንዳይቀር አስችሎታል።

ይህም ማለት ለዋናው ስራ የታመነ በሚፈቅድለት መንገድ በኩል የማይጎዳና የደራሲውን ፍልስፍና የማይጋፋ ታሪክ የማውጣት ሙብቱን የተጠቀመበት ታሪኩን ከማስወጣት በሌሎች ገጸባህርይ የሚባለዉን ንግግር የተወገዱ ገጸባህርይ ከሆኑ በሌሎች ገጸባህርይ ሀሳባቸው ተገልጾ እንዲያልፍ አስችሏል ይህም ደግሞ የደራሲዉን ፍልስፍና ሀሳቡ ተነግሮ እንዲያልፍ አድርጎትል።

በቀጣይም በመጀመሪያዎቹ ክፍል ተገልጾ ማለፍ መቻል እያለበት ሳይገለጽ የታለፈው ሀሳብ ምንድን ነው? ብለን ጥያቄ ስናነሳ

በዛብህ በድራማው ላይ በዋሸራ፤ዙራምባ ኋላም ላይ ደብረወርቅ ላይ አርፎ ወደ ዲማ ገብቶ ከአለቃ ክንፉ ጋር ተገናኝቶ ነበር ያቆመ፤ በመጽሀፉ ላይ የተገለጸው ደግሞ በዛብህ በዋሸራ፤ዙራምባ ያለፈበት ሁኔታ በ አጭር ገለጻ ብቻ ነበር የተገለጸው በተጭዕማሪም በደብረወርቅ ቆይቶ ት/ቱን በሚያስቀጥልበት ወቅት ያረፈባት ሴትዮ በእመት ጠጅቱ ቤት ነበር ከእሳቸው ጋር አርፎ ተምሮ ሲጨርስ ነበር ወደ ዲማ አቅንቶ ከአለቃ ክንፉ ጋር የተገናኘ በድራማው ላይ ግ ን ከ እመት ጠጅቱ ጋር ያለዉን ቆይታ ተቀንሶ እናገኘዋለን።

በአጠቃላይ በድራማው ላይ የነበረዉን የጽሁፍ ይዘቱን ከመቀነስ እና ከመጨመር አንጻር ሲታይ ያለበት ሁኔታ ጥሩ

ነው።በተጨማሪም በጥሩ ጎኑ በድራማው ላይ ገጸባህርያቱ የሚጠቀሙት ቃለ ንግግር ከመጸሀፉ ቃልበቃል ምንም ሳይበረዝ በአብዛኛው የድራማው ክፍል ላይ ተገልጾ እናገነኘዋለን፤ለየት ያለ ቃለ ንግግር ቢኖርም ገጸባህሪው ቃልበቃል በመጽሀፉ ላይ ብሎ ያላለፈ እንኳን ቢሆን በልቦለዱ በሆነ ሁኔታ ላይ የተገለጸዉን ጽሁፍ ለገጸባህሪይው ሲጠቀምበትት ይስተዋላል።

### 3.3.3 መቼትን ወደ ድራማ መቼት ከመለወጥ አንጻር

የፍቅር እስከ መቃብር ረጅም ልቦለድ መቼቱን ወደ ድራማው ወደ ሚታየው ከመለወጥ አንጻር ከተጻፈው በላይ እጅግ በጣም ጥሩ በሆነ ሁኔታ አቅርቦልናል። በልቦለዱ ውስጥ አንዳንድ ቦታዎች በሰዓቱ መኖርን የሚሹ ምልከታን ይጠይቃሉ፤ይህም ማለት ፍቅር እስከ መቃብር በጥቅሉ በ1960ዎቹ የተጻፈ እንደመሆኑበዚያን ጊዜ ሊኖሩ የሚችሉ ቁሳቁስ ቦታውን የሚወክልልን፤የማ/ሰብ መስተጋብር፤ባህል፤ዘዬ፤እንዲሁም የተለያዩ ሁኔታዎችን በሚታይ መልኩሲቀርብ በመቼ እና በየት የሚለውን ጥያቄ ያነሳል። ይህም ጥያቄ ሲነሳ ደግሞ ድራማው እጅግ አጥጋቢ መልስ ሁኖ ተቀምጦልናል።

በድራማው የተገለጹት የተለያዩ ቦታዎች ለአንባቢ በትውስታ እና በንግርት እንዳያልፍ አድርጎታል።ይህን ስንል በዛብህ ከቤተሰቦቹ ተለይቶ በተለያዩ ቦታዎች እየዞረ ሲማር በመጽሀፉ ላይ በቃል ብቻ ነበር የተገለጸው ለ አብነት ያህል እንመልከተው

*በዛብህ ' ወላጆቹን ' ከድቶ ፡ ማንኩሳን ፡ እንደለቀቀ ፡ ዋሸራ ' ወደምትባል ' አገር ' ሄደ ፤ ቅኔ' ቤት ፡ ገባ = በዋሸ ራም ፡ አንድ ፡ አመት ፡ እንደቆየ ፡ ቅኔ ተቀኝቶ ፡ ዝማሬ ፡ መዋ ሴት ፡ ለማሄድ ፡ ወደዙር ' ' አምባ ፡፡ ፡ ሄደ ሄደ ። ። ዙር ዙር ' ' አምባ እምባ ' ሁለት፡ አመት' ያክል ' ቆይቶ ዝማሬ መዋሲትና" ጽህፈት፡ ካወቀ፡ 1 1 በሁዋላ ' ደብረወርቅ ፡ እምትባል ፡ አገር ፡ ሉዲስ ፡ የመጻህፍ ፡ መምህር ' ከጎንደር ፡ መምጣታቸውን ' ስለሰማ ፡ ወደዚያ ፡ ሄዶ ፡ መጻህፍ ' ለመቀጸል ፡ ወሰነ ።*

እንዲህ ተገልጾ የምናገኘው በዛብህ የረገጠበት የወረደበትን መንገድ ተደራሲው በምናብ ከመሆን ባሻገር በድራማው ላይ በዋሸራም ሆነ በዙራምባ የቆየበትን ሁኔታ በጥሩ መቼት ተገልጾ እናገኘዋለን

በመቀጠልም ውድነሽ በጣሙ በመጸሀፉ ላይ በየመንደሩ በየሰፈርተኛው “ባሎችን የፈጀሽን ፈጂ” ብለው ሲዘልፏት አስታውሳ ለነፍስ አባቷ በመጽሀፉ ላይ

*“ እሱስ ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ብቻ ፡ የሰው ፡ መላስ ፡ ከሳት ፡ የበለጠ ፡ ያቃጥላል ። በቀደም ፡ እዚያ ፡ እሰንበቴው ፡ ከብላታ በዬነ' ባለቤት፡ ጋር ፡ ባንዳንድ ፡ ትንሽ ፡ ነገር ፡ ተከራከረን ፡ የምትረታ ፡ ስትሆን ፡ ጊዜ ፡ ቶሎ ፡ ብላ ፡ እኔን ፡ ስትነካኝ ፡ የሚያሳምመኝና : የሚያሳፍረኝ ፡ ቁስል ፡ ፈልጋ ' " እንቺ ፡ ባሎችሽን ፡ የፈጀሽ ፡ የባል ፡ በሽታ ፡” ብላ ፡ በተሰበሰበው ፡ ህዝብ ፡ ፊት ፡ ሰደበችኝ ።” አሉና ፡ እመት ፡ ውድነሽ ፡ ያነ ለት ' ሰው ፡ ሁሉ ፡ እሳቸውን ፡ እያዩ ፡ የሳቀውና ፡ ያሽሙዋጠ ጠው ፡ ታያቸውና ፡ እንደገና ፡ እንባቸው ፡ ባይናቸው ፡ ቸርፈፍ ' አለ ።* በዚህ ክፍል ላይ የሰፈረዉን ገለጻ በድራማው በክፍል 4 በ 2ኛው ደቂቃ ከ 30ሰከንድ ላይ ወደ ኋላ ወስዶ በቦታው አስገኝቶ ድብቡ እንዲጋባብን ያደርረገበት መንገድ የሰርጉን የዘመኑን የሰርግ ሁኔታ ቦታ አቀማመጥ የተገለጸበት መንገድ ጥሩ ነበር።

ለምሳሌነት ከላይ ያለውን ለማየት የሞከርን በመጽሀፉላይ በአንድ ወይም በሁለት መስመር እንደዚህ ሁኖ...ተደርጎ.....አለፈ የመሳሰሉትን ምልከታ በኛ ላይ ያስመለከተን በድራማው ላይ ግ ን በሚገብ መልኩ ለዕይታ የበቁትን ነው።

እንዲሁም ደግሞ በተጨማሪ በድራማው ላይ የፊታውራሪን መሸሻ መኮንን፤ ባላባትነትን የኑሯቸዉን ሁኔታ የአገልጋያቸዉን ብዛት በቤቱ ውስጥ ያለዉን ተድላ የቤቱ የአቀማመጥ ሁኔታ ያሳየበት መልኩ አሪፍ የሚባል ነው።

በመጨረሻም በድራማው ላይ የተገለጹት መቼቶች ከመጽሀፉ ካሉትም ሆነተነግረው ያለፉትንም ያላለፉትንም ነፍስ ዘርተው አዋህደው ያቀረቡበት መንገድ ስራቸው ጥሩ መሆኑን ያሳያል።

### 3.3.4 ታሪኩ ከዋናው ታሪክ ጋር ያለው ተዕማኒነት

የፍቅር እስከ መቃብር ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማከዋናው ፍቅር እስከ መቃብር ርረጅም ልቦለድ ጋር ተከታታዩ የቴሌቪዥን ድራማ ምን ያህል ለዋናው ታሪክ አመኔታዉን አስቀጥሏል ወይስ አጉድሏል የሚለዉን ለማየት በሴራ፤በገጸባህርያት በሁለቱምየጥበብ  እልፍኝላይ አደራደር እንዲሁም በጭብጥ ዙሪያና የመሳሰሉትን እንዴት እንደተገለጹ እናያለን።

#### 3.3.4.1 በገጸባህርያት ዙሪያ

በገጸባህርያት ዙሪያ ላይ እንትና እና እከሌ ብለን በሁለቱም ወገን ያሉትን እጅግ ብዙ ገጸባህርያት መጥቀስ አንችልም። ለምን?ም/ቱም በተከታታዩ የቴሌቪዝን ድራማ ላይ አሁን ላይ ያልሰየማቸዉን የታሪኩ አካላት ወደ ኋላ አካባቢ ሊከስትልን ስለሚች ባይሆን ግን ል በጥቅሉ ከተቋጩ ታሪኮች ወደ ኋላ ዙሮ ከማያያቸው ታሪኮች አንጻር ምን እንደሚመስሉ እንመልከት ።
በድራማው ወደ ኋላ መለስ ብሎ ከማያየው ታሪክ ዉስጥ አንደኛው በዛብህ ለት/ት ብሎ የረገጣቸዉን ሀገርት ነው እንግዲህም በእነዚያ ጊዜ ቆይታው የገጸባህርያት ሁኔታቸዉን ስንቃኝ  እንግዲህ በዛብህ በዋሸራ፤ዙራምባ በስተመጨረሻም ላይ ታሪኩ ያቆመው ዲማ ከአለቃ ክንፌ ጋር ሁኖ ሳለ ነበር፤ በመጀመሪያ ላይ ከጠቀስናቸው የሱ ማዳረሻ ትዕይንቶች መካከል ይመጡ የነበሩት የተለያዩ ገጸባህርያት በመጽሀፉ ዉስጥ ምንም ቦታ የተሰጣቸው አልነበሩም የሌሉትን መጨመራቸው የታሪኩን ተዕምኒነት ያጎድላል ማለት ግ ን አደለም ለምን? ም/ቱም የተገለጹት ገጸባህርያት ታሪኩን የሚያጉዙልን የመጽሀፉን ይዘት ተከትለው ምርኩዝ፣ድጋፍ ለተደራሲያን ትክክለኛን ምስለት ሊያሳዩ ስለቻሉ ጥሩ ነበሩ ማለት ይቻላል እንዲሁም በተቃራኒው ወደ ዲማ ከመድረሱ በፊት በደብረወርቅ ቆይታው ከአንዲት እመት ጠጂቱ የተባለች ገጸባህርይ ጋር ነበር ቆይታዉን ያደረገው ደብረወርቅ የነበረዉን ቆይታ ሲጨርስ ነበር ወደ አለቃ ክንፉ ዲማ መንገዱን ያቀናው በድራምው ጊዜ ግ ን ከ አለቃ ክንፉ ጋር መገናኘቱ እርግጥ እንደመሆኑ ከመገናኘቱ በፊት ግ ን ከእመት ጠጅቱ ጋር መገናኘት እያለበት አለመገናኘቱ እመትጠጅቱ አለመገለጥጿን ያሳየናል ምናልባት በቀጣዮቹ ተገልጻ ልታልፍ ትችል ይሆናል ነገር ግ ን የድራማው ታሪኩ አሁን እስካለበት ድረስ የእርሷ ቆይታዋ አሁን በድራማው ካለበት ክፍል ስለሚስተካከል ሳትገለጽ ማለፏ ድክመት ሁኖ እናገኘዋለን።
እንዲሁም በተጨማሪ በመጽሀፉ በስም ደረጃ ተጠቅሰው የምናዉቃቸው ገጸባህርያት በድራማው ላይ በአካል ተከስተዉልን የተሟላ ነገር ሲያሳዩልን ይስተዋላል በመጸሀፉ ላይ በገጽ13 ላይ እመት ውድነሽ ለነፍስ አባቷ በሰንበቴው የደረሰባትንበደል ስትገልጽ ያደረሱባትን ፌዝ ሳቅ በድራማው ላይ ከዋኒዎቹ የየራሳቸውን ገጸሃብርይ ይዘው ነፍስ ዘርተው በሰርግ ቦታ ላይ በድራማው ላይ ይመለከታሉ። እንዲሁም በእነፊታውራሪ መሸሻ ቤት ዉስጥ የሰብለን አገልጋይ ሀብትሽን አጥፍታ እናቷ ስትመክራት በምስል የተከሰተው ሰብለ ሊጅ እያልለች ከሀብትሽ ጋር ያሳለፈችውን ጊዜ በድራማው ላይ አዲስ ገጸ ባህርይ ሁነው መገኘታቸዉን ያሳየናል አዲስ ቢሆኑም ለዋናው ታሪኩ ምርኩዝ ድጋፍ የሚሆኑ ገጸባህርይ ሁነው ይገኛሉ። በድራማው ላይ ከላይ የጠቀስናቸውን የተጨመሩት ግጸባህርያትከትክክለኛው ከመጽሀፉ ጋር ካሉት ምንም ቅራኔ የለባቸዉም እንዴዉም ዉበትን ጨምሮለትል። እስካሁን የቀረቡትን በድራማው ክፍል ቆይታ ውስጥ ካሉት ሌሎች ጋር እነርሱ የተሳሉበት መንገድ ያላቸው የማንነት ገለጻ ከተሳሉበት መንገድ አንጻርተዕማኒነትን ያሟሉ ናቸው።

### 3.3.4.2 በጭብጥ ዙሪያ

በጭብጥ ዙሪያ መጽሀፉን አጠቃሎ ያነበበ ሰው መልዕክቱን መረዳቱ አይቀሬ ነው መጽሀፉን አንብቦ እንደጨረሰ ሰው እና ጭብጡን እንደሚያዉቅ ሰው የቴሌቪዥን ድራማው እያዳራሰ እስካለበት ክፍል ድረስ ድራማው ጭብጡን እስካእበት እንዴት እያንጸባረቀ ነቅ የሚለዉን እንመልከት
ይህን ስንል በፍቅር እስከ መቃብር ረጅም ልቦለድ ላይ በፍቅር ሰይሞ ሁለት ወጣቶችን ከፊታችን ወክሎ በኧነርሱ ላይ ላይ ቢያስመስለዉም ነገሩ ግ ን ወዲህ ነው... የበዛብህን አመጣጥ የሰብለን አስተዳደግ በሁለቱ መሀከል የሚፈጠርባቸዉን ጉድ ስንመለከት መልሱ ቁጭ ብሎ እናገኘዋለን ማለትም በዛብህ የታችኛው ም/ሰብ የገበሬዉን ዝቅተኛዉን ሲወክልልን ሰብለ ደግሞየባላባት የገዥዉን ም/ሰብ ወክላልን እናገኛለን። ይህም ጠቅለል ስናደርገው በጊዜው የነበረዉን የፊዉዳሊዝም ስርዓት፤የዘመኑን አስተሳሰብ፤ባህል፤የተለያዩልምድ ወጎች በሁለት ወጣቶች ሽፍኖ በዘመኑ ይደርስ የነበረዉን መልዕክት አስቀምጦልናል።
ከላይ ከገለጽነዉም አንጻር የተከታታይ ቴሌቪዥን ድራማዉም ከላይ ያየነውን ጭብጥ በማሳወቅ ደረጃ ለዋናው ጽሁፍ ተዕማኒነቱ ምን ያህል ነው ስንል.... ለአብነት ያህል መጀመሪያ ላይ ቦጋለን እንመልከት ቦጋለ ደከመኝ ሰለቸኝ የማያዉቅ ታታሪ ገበሬ እንደመሆኑ ስራዉን ደከመኝ ሳይል ሲሰራ ይታያል ነገ ግ ን ከስራው ባለ መሬቱ ሲያባርረው የገከጸበት መንገድ የጊዜዉን ስርዕት በመጀመሪያዎቹ ክፍል ላይ ሊያሳዉቀ ችሏል ማለት እንችላለን የዘመኑን ባህል ወግ ልማድ ወግ የተሰኘዉን ደግሞ በ እመት ዉድነሽ በሰርግ ቤቱ ላይ ያደረሱባትን በደል ማሳየታቸውይጠቁምልናል።
እንደ አጠቃላይ ታሪኩ ከዋናው ታሪኩ ጋር ያለው ቁርኝነት ምን ይመስላል ለሚለው በጥቅሉ አንድን የጥበብ ስራ ወደ ሊአላ የጥበብ ስራ ስናላምድ ሊፈጠር የሚችል ብዥታ መኖሩ የግድ ነው።ከዚህ በተጨማሪም ግ ን የተከታታይ ቴሌቪዥን ድራማው እስከደረሰበት ክፍል በውስጡ የደረሰበት ዋናዎቹ ብለን ያየናቸዉን ገጸባህርያት እና ጭብጡ ከልቦለዱ ጋር ያላቸው አመኔታ እጅግ በጣም ጥሩ ነው። ምክን ያቱም የታሪኩን ይዘት በማይጣረስ መልኩ ለመጽሀፉ ቅርጽ ዉበት የተጨነቀ፤የሆ ነው፤ በተከትታይ ቴሌቪዥን ድራማው ውስጥ የተገለጹት/የተጨመሩት ገጸባህርያትም ንግግራቸው በክፍል ወይም ምዕራፍ ይለላይ እንጂ መጽሀፉ ላይ ያለ ንግግር ነው በመጨረሻም አቀራረቡ ጭብጡን ያልዘነጋ የታሪክ ፍሰቱን የጠበቀ ድራማ ሁኖ እናገኘዋለን።

## 3.4 በማላመድ ወቅት የሚያጋጥሙ ችግሮች

### 3.4.1 የትረካ አንጻር

የፍቅር እስከ መቃብር ድራማ ከውርስ ስራ አንጻር ወደምስልነት ተሻግሮ ወደ ድራማ የሆነበት አካሄድ በውስጡ ከአንዱ ወደ አንዱ ሲሻገር መሠረታዊ የሆኑ ጉድለቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ። ይህም አንዱ አተራረከነው በመጽሀፍ ላይ የተጻፉ /የተገለጹት/ የትርከት አይነት ወደ ፊልም/ድራም ሲመጣ አዳጋች ይሆናል።
በፍቅር እስከ መቃብር ተከታታይ ድራማ የደረሰበት አራት ክፍል ድረስ በመጽሀፉ ዙሪያ ከአራቱም አንጻር ስንመለከት በመጽሀፉ ላይ ብዙሀኑየተገለጸው በሁሉን አወቅ ወይንም ደግሞ በ3ተኛ መደብ የአተራረክ ዘዴን የተጠቀመ ነው ይህም ደግሞ ወደ ምስል በሚሻገርበት ጊዜ ጥሩ የሆነን ዕይታን እንዲይዝ አስችሎታል። በድራማው በክፍል አንድ ማብቂያ ላይ

በልቦለዱ ላይ እንደተገለጸው በዛብህ ለብቻው ሁኖ ሳለ ያለበት ሁኔታ በአንደኛ መደብ የአተራረክ ስልት "'እኔ" እያለ ሲተርክ ይመለከታል ይህም በመጽሀፉ በምዕራፍ4 በገጽ36 ላይ ተገልጾ ይታያል።
በጥቅሉ በድራማው በደረሰበት ክፍል እስከ መጽሀፉ የተገለጸበትድረስ፤በመጽሀፉ የነበሩትን የ3ተኛ መደብ የአተራረክ ስልት እና የ1ኛ መደብ የአተራረክን ስልትን በድራማውም ላይ ተገልጾ መገኘቱ በመጽሀፉም ያለዉን ለዛ በድራማዉም ላያ ብሮ ለዛ ያለው አካሄድን እንዲይዝ አስችሎታል።

### 3.4.1.1የአተራረክ ቅርጽ

የአተራረክ ቅርጽን ስንመለከት በሁለት የተለያዩ ሚዲየምላይየተለያየ አይነት የታሪክ ንርት ያለው የታሪክ ፍሰት መከተላቸው የማይቀር ነው።ይህም በልቦለድ ጊዜ በየምዕራፍ እየተከፋፈለ ከአንዱ ትዕይንት ወደ ሌላኛው ትዕይንት ፍሰቱን ጠብቆ መቅረቡ ይታወቃል። ድራማ ላይ ስንመጣ ግ ን ምስል ከሳች እንደመሆኑ መጠን ባሻው ሰአት የፈለገዉን የትዕይንት ቦታ ሊዳስስልን ይችላል በተጨማሪም ድራማ የታሪክ ፍሰት አካሄዱ በምዕራፍ ተከፍሎ በዉስጡ ደግሞ በክፍል ተከሽኖ እንደሚቀርብ ይታወቃ ታዲያ በዚህ ጊዜ በልቦለዱ ላይ የቀረበዉን ፍሰት ተከትሏል ወይ ስንል? መልሳችን በፍጹም ይሆናል ም/ቱም ድራማውየተከተለው ዘዴ ለመጽሀፉ ታምኖከታሪኩ  ሳያፈንግጥ መላመድ ስለሆነ እንጂ የሎለዱን ፍሰት እግር እግር መከተል አደለም አካሄዱ በጥቅሉ ድራማዊ ፍሰቱ የታሪኩን አምድ የተከተለ ነው ማለት እንችላለን።

### 3.4.1.2 የዕይታ አመራረጥ

በዕይታ አመራረጥ ላይ በፍቅር እስከ መቃብር ድራማ ላይ አዘጋጁ ያቀረበልን ምስል እጅግ በጣም አሪፍ ነው ማለት ይቻላል።ም/ቱም ለአብነት ያህል በድራማው የቀረቡትን የተለያዩ ድርጊቶች ሚከናወኑበትን ቦታ ሀገር ሁኔታ ድባብ ስንመለከት በሰአቱ ያለን ያህል ሁነን የድራማው አካል እንድንሆን አድርጎ ነው ያቀረበልን በእመት ውድነሽ እናአያ ቦጋለ ያላቸው የኑሮ ድረጃ የሚኖሩበት ቤት ያቀረበበት መንገድ እንዲሁም የባላባቱ ፊታውራሪ መሸሻ ቤቱ የቀረበበትመንገድ በዙሪያው የነበረው ድባብ እንደ ባላባትነቱ የቀረበለት ያለበት ቤት ስፋት ሁኔታን ብንቃኝ እንዲሁም በተጨማሪ በዙሪያ የመንደሩ ሑኔታ ምን ይመስላል ስንል በቅዳሴ በሰርግ በስራ ቦታሁሉ ተወክለው ያገኘናቸው የተለያዩ ቦታዎች ዘመኑን የከሰቱልን መንገድ ጥሩ ነበር።
እንዲሁም ደግሞ በቦታው ላይ ጊዜዉን ወክለው በጊዜው የደረጉትን ነውገሮች የከዉኑልን ገጸባህርያት የቀረቡበት የአልባሳት ሁኔታ ስናይየባላባት ወገኑን እንደ ባላባት ዝቅተኛው ማ/ሰብ እንደየአቅሙ ያለበትን ሁኔታ በአልባስ ሲገለጽ ጥሩ የሚባል ነው ከአልባጽ በተጨማሪም የተለያዩ የቤትም ሆነ ዉጭ ላይ ያሉ ቁሳቁሶች ወደ ድራማው ላይ የመጡበት መንገድ የተሰሃአቸው ዉክልና ጊዜዉን ደምቀዉልን አልፈዋል ማለት እንችላለን
በመጨረሻም ልቦለዱን አላምደው ወደ ጽሁፍ ቀይረው ለአኢጋጁ ሰጡት እሱስ የድራማዉን ድራማዊ ገጽታ በምን መልኩ ይዞልን ቀረበ/ሲኒማቶግራፊው እንዴት ነው ስንል አዘጋጁ ወደ ተደራሲ ያቀረበበት መንገድ የዘመኑን ድባብ፤ዘይቤ፤ወግ፤ልማድ ቀርጾ ከማስተላለፍ ይልቅ ድባቡን በማጋባት ረገድ የቀረበበት መንገድ ጥሩ ነው በድራማው

የታየው ዕርጋታ የቀረበበት የቀለም ሁኔታ የመጽሀፉን አስዛኝ ዘዉጉንም ይጠቁመናል የዘመኑን ድባብም ያዋህድልናል።

### 3.4.2 የተደራሲው ስሜት

የፍቅር እስከ መቃብር ተከታታይ ድራማ ለተደራሲው ስሜት ከማጉደፍ ይልቅለተደራሲው ዕይታ፤መስመር የሆነ ድራማ ነው! ለምን? ም/ቱም ተደራሲው ወይም ደግሞ የመጀመሪያ ይዘቱ የመጽሀፍ አንባቢያን መጽሀፉን በሚያነቡ ወቅትብዙ አይነት የምናባዊ አድማስ ምልከታ ያስፈልጋቸዋል።በድራማ መልኩ ሲቀርብ ግ ን የነሱን የምናብ ምልከታ ቅልብጭ ባለ ከዘመኑ ጋር የተዋሀደ የተደራሲዉን ስሜት የማይጣረስ ድራማ ሁኖ እናገኘዋለን።
አንባቢው መጽሀፉን በሚያነብ ወቅት የበዛብህን ተክለ ሰዉነት ከማሰብ ይልቅ ፤የሰብለን ፈገግታ ከማለሙ  ይልቅ አዳጋች የሚሆነው ዘመኑ ሊላበስ የሚችለውዉን ገጽታማገናዘብ ነው።በድራማዉም ምስሉን ይዞ ሲከሰትልንበመጀመሪያው ክፍል ከአንድ ሚሊዩን በላይ የሆነን ዕይታ ሊያገኝ ችሏል ይህም የሚያመላክተን ተደራሲው ምን ያህል ድራማዉን ወዶ እና ተመችቶት ሊመለከቱት እንደቻሉ ነው። የድራማውም አዘጋጅ ሰውመሆን ይስማው በአርትስ ቲቪ በነበረው ቃለ መጠይቅ “ሁሉንም ደስተኛ ማድረግ እንደማይቻል”ተናግሯል ቢሆንም ግ ን ደስተኛው ተደራሲ ሚዛን ደፍቶ እናገኘዋለን፤አዘጋጁም የተለያዩ የጊዜዉን ሁኔታ የገለጸበት መንገድ፤የተለያዩ በድራማው ላይ የተካተቱት ቴክኒኮች እጅግ ተወዳጅ፤ማራኪ በሆነ መልኩስለቀረበ የተደራሲዉን ስሜት ከማስከፋት ይልቅ የዕይታ እርካታ ነውማለት ይቻላል።
በተጨማሪም የተመልካች ቅቡልነት ምን ይመስላል? ሚለውን ስንቃኝ ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማው ከመጀመሪያዉንም ምስል ነክ እንደመሆኑ ተወዳጅ ቢሆንም የረጅምም ልቦለድ መጽሀፉም ወደ ምስል ሜዲየ ሲቀየር ተቀባይነትን አግኝቷል ማለት ይቻላል።እንዴት? ስንል ተእመልካች ወይም ተደራሲ የሱን ቅቡልነት ማረጋገጥ የምንችለው በመጀመሪያም ድራማው በወጣ ሰሞን የተመልካቹን መጠን በመመልከት እንዲሁም በተጨማሪ በተለያዩ ሶሻል ሜዲያዎች ስለ ድራማው የተባሉትን ሀሳብ አስተያየት በመቃኘት የእነርሱን ዉዴታ ማወቅ ይቻላል፤ድራማው በወጣ ሰሞን ሳምንት ባልሞላ ጊዜ የነበረው ተመልካች ቁጥራዊ መረጃ እንደሚያሳየን ከ500ሺህ በላይ እይታ ነበረው እዲሑም በተለያዩ ሜዲያዎች ላይ የነበረው ሀሳብ ድራማው ከተቋረጠበት ይጀምርልን የተሰኘ ነበር እንጂ ቅራኔን የፈጠረ አልነበረም።

### 3.4.3 ፍልስፍናን ከማንጸባረቅ

በዚህ ዙሪያ ላይ በሁለቱም ወገን ስንቃኝ የድራማው መቋጨት ግድ ሊሆንብን ነው።ቢሆንም ግ ን በመጽሀፉ ካለው ፍልስፍና የመጽሀፉ ምልከታ አንጻር የድራማው ጅማሬ እንዴት ነው ብቻ የሚለዉን ለማየት እንሞክር ፤በዋነኝነት ፍቅር እስከ መቃብር መጽሀፉ በጊዜው የነበረዉን የፊዉዳሉን ዘመን፤ባህል፤አስተሳሰብ እንዲሁም የአኗኗር ዘይቤ በዘመኑ የነበረዉን ምን ይመስል እንደነበር ሊዳሥ ስልን ሞክሯል። “ፍቅር እስከ መቃብር”ተሰኝቶም በዛብህ እና ሰብለ የተሰኙ ሁለት አፍላ ወጣቶች በማዕከላቸው የሚንበለበል ፍቅር የተባለ እቶን ውስጥ ዘፍቆ ለተደራሲያን ስለ ሁለቱ ፍቅርብቻ ትኩረቱ አስመስሎ በሽፋን መስሎ አሻግሮ ማየት ለቻለ ግ ን መልዕክት ያስቀመጠ ድንቅ መጽሀፍ ነው።በዛብህ እና ሰብለ ምንም እንኳን ሁለቱ በፍቅር ቢወድቁ አብረው መሆን የማይችሉበት 'ጉድ” የተሰኘ በዘመኑ የነበረን የፊዉዳል አገዛዝ ፍቅራቸዉን እንዳያስቀጥሉ መሰናከል ይሆንባቸዋል። ሁለቱ ገጸባህርያት እንዲሁ ወንድ እና ሴት የሆኑ ብለን ካለፍን ችግር

ነው! ምክንያቱም እኒህ ገጸባህርይ የሁለት ዐለም ሰዎችን ወክለው የአንድን ማህበረሰብ አወቃቀር የሚያሳዩ ናቸው። የሴቷ ገጸባህሪ ወይም ሰብለ ወንጌል ከባላባት ወገን በዛብህ የተሰኘው ደግሞ ከአነስተኛው ማህበረሰብሰብ ክፍል የሚወክልልን በሁለቱ መሀከል የሚመጣንጉድ የሚያመለክት መጽሀፍ ነው።
ከላይ ለማየት በሞከርነው መጠን የሁለቱ የባላባትናየአነስተኛው ክፍል በድራማው እንዴት ጅማሮዉን ያሳያል ብለን ስንመለከት የበዛብህአባት ከአሰሪው ጋር በነበረው ግ ንኙነት ለስራ ተቀጥሮ ወዲያውም ለስራ በተባረረበት ጊዜ በደል አንድ ብሎ ይጀምራል። እንዲሁም በእነ ፊታውራሪ መሸሻ ቤት የሚፈጽሙ ነገሮች ሀሳቡን ይደምቅልናል።ከአገልጋዮቻቸው ጋር ያላቸዉን መስተጋብር ስንመለከት ማለት ነው።በጥቅሉ በድራማው ያለው ጅማሮ አሪፍ የሚባልና የመጽሀፉን ጥሩ በሚባል ደረጃ ማስቀጠል የሚችል ነው ማለት እንችላለን።

## 3.4.4 የገጸባህርያት አሳሳል

በፍቅር እስከ መቃብር ረጅም ልቦለድ ውስጥ ረጅም ልቦለድ እንደመሆኑ መጠን በርካታ ገጸባህርያት ተገልጸው ይታያሉ። እኒህም ገጸ ባህርያት ወደ ድራማው በሚመጡ ጊዜ የተለየ ነገር አይኖርም። ገጸባህርያቶቹ በልቦለዱ ላይ እንደሰፈረው መገለጻቸው የማይቀር ነው። ማለትም ገጸ ባህርያቱ በቀለም፤በቁመት፤በዕድሜ ይህን ያክላሉ ተብሎ የተካተተዉን መመጽሀፉ ስር ነፍስ ዘርተው እናገኛቸዋለን።
በዋናነት አጥኝው ሊመለከት የፈለገው በጽሁፍ፤በቃላት ገጸባህርያቱን ከዉስጠኛው ማንነታቸው በመነሳት ለውጨኛው ምን አይነት ጋጽታ ይዘዉልን መጡ ሚለዉን ነው ይህን ለመዳሰስ እንደ ብነት አያ ቦጋለን እንመልከት በመጽሀፉ ላይ በገጽ20"ቦጋለ ከድሆች ወገን ተወልደው በድህነት ያደጉ፤ከህጻንነት እስከ እኩል እድሜ ችግር ያልተለያቸው ከችግር ጋር ሲታገሉሲጥሉት ሲጥላቸው አብረው የኖሩ ቆዳቸው ጠንክሮ ስድብ ይሁን ቁጣ የማይዘልቀው ነበሩ..."እንዲህ ሲል በአጭሩ የገለጻቸዉን ድራማዉም ላይ በክፍል4 ላይ በዙሪያው ከነበሩት ጓደኞቹ ጋር የነበረው መስተጋብር በኋላ ላይም ወደ ቤቱ ሄዶ የሚመገበው ደረቅ ቂጣ፤ከአሰሪው ጋር ያለው ንግግር፤ከእመት ውድነሽ ጋር ያለው ንግግር...የመሳሰሉትከላይ ያየነዉን የእርሱን ገለጻ ይወክልልናል።
በዋነኝነት በታሪኩ ዙሪያ ላይ በመጽሀፉ በዛብህናበሰብለ መዘዝ ዙሪያ ላይ ማጠንጠኑ የታወቀ እንደመሆኑ በድራማው ወቅት ላይ በሚኖራቸው የምስል ቆይታ ለሁለቱኡ የተሰጠዉን አጽዕኖት በሌሎች ዘንድ በሚኖራቸው መስተጋብር ለእነርሱ የሚሰጣቸው ቦታ ሻል ያለ በመሆኑ ሁለቱም ተስለው የተገኙበት መንገድ ጥሪ የሚባል ነው።

## 3.3.5 ቃለ ንግግር መረጣ

ለንባብ የቀረበና በካሜራ እይታ ውስጥ ለሚሆን ስራ የሚቀርበው የጽሁፍ አቅም እንደይ ጽሁፉ ዝይነት ይለያያል የቴሌቪዥን ድራማዉም ከ ልቦለዱ ወደ ድራማው ቃላትን የመረጠበት መንገድ በካሜራው የገለጸበት መንገድ እንዴት ነው ብለን ስናይ በድራማው ላይ በ ክፍል አንድ ማብቂያ ላይ የበዛብህ እናት መቀነቷን ፈልጋ ማጣቷ ሊያስተላልፍልን የፈለገው የራሱ የሆነ መልዕክት አለው ይህም በካሜራ ቋንቋ ምቹ በሆነ ሁኔታ ቀድመው ዕዉቂያ ሰጠውን ማለፋቸው ጥሩ ነገር ነው። በተጨማሪም በክፍል 4 ላይ አያቦጋለ ከሚስቱ ጋር ተጨቃጭቀ ወጥቶ በመጽሀፉ ከራሱ ጋር የሚያነበንበው በድራማው ላይ ደሞ ሁለት ሰዎችን የወከለበት መንገድ ጥሩ የሚባል ነው። በጥቅሉ ለንባብ ከቀረበው ልቦለድ ወደ ምስል ከሳች ሲመጣ

የተጠቀማቸው ካሜራዊ ቋንቋዎች እጅ በጣም ጥሩ የሚባል ነው።

## ምዕራፍ አራት

## ማጠቃለያ

አንድን የኪነጥበብ ስራ ወደ ሌላ የጥበብ ጓዳ የማላመድ ሂደት ከላይ ያየነውን ይመስላል።በሀገራችን የተላመዱ ስራዎች ብዙ ጊዜ አይስተዋሉም፤ከሀገራችን ወጣ ስንል ግ ን የተለያዩ ተወዳጅ የጽሁፍ ስራዎችን በማላመድ ስራ ውጤታን ሲቀዳጁ ይስተዋላል፤ ይህም ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማ ስራ ለብዙዎች ጀማሪ ፊልም ሰሪ በርን እንደሚከፍት አያጠራጥርም።

አንድ የሚያላምድ አካል ልቦለድን ወደ ፊልም በሚያላምድ ጊዜ ለስራው የተለያዩ ስልቶችን መጠቀሙ እርግጥ ነው፤በዋነኝነት በምዕራፍ 3 ላይ ለትንታኔ ያቀረብናቸው ሂደቶች እንዳሉ ሁሉ ይህንንም የተላመደ ስራ ከስልቶቹ አንጻር

ሊገጥሙት ከሚችሉት ተግዳሮቶችም አንጻር የፍቅር እስከ መቃብርን ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማ ከተጠቀሱት ስልቶች አንጻር ሂደቱ ምን ይመስላል የሚለዉን እስከደረሰበት ክፍል ተገምግሞ ገርቧል።

የፍቅር እስከ መቃብር ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማ ባሉት ስልቶች ሂደቶች አኳያ ስራው የተሳካ ሽግግር አድርጓል ማለት እንችላለን።በሀገራችን ተላምደው የቀረቡት ፊልሞች አብዛኛውን ከአጫጭር ልቦለዶች ነው ፤የፍቅር እስከ መቃብር ግን ለሀገራችን በረጅም ልቦለድ የማላመድ ሂደት ግን ስኬታማ በሆነ የለውጥ ሂደት ፈር ቀዳጅ ነው ማለት ያስችለናል። ወደፊትም በዚህ በማላመድ ስራ ላይ መጀመር ለሚፈልጉ ጀማሪ ፊልም ሰሪዎች ፤አዘጋጆች ይህ ስራ እጅግ በጣም መስመር የሚያስይዛቸው እና በስራቸው ላይ ውጤታማ የሆነ ስራን ይዘው እንዲቀርቡ የሚያስችል ድንቅ ስራ ነው።

## ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው

1.the relationship between two things

when one thing can represent another (Montgomery, 1992, p. 193). The term sign refers to the arbitrary relationship between two things, for example, a word “flower” can be a sign of a flower; also, a picture of a flower

can be an icon of the flower which shows a less arbitrary relationship between the two

2. Since the camera can only show its appearance, the film must use other methods to express people's emotions

3 It is clear that the sound of the film can greatly improve the audience's perception. If the audience of the film can get the information from both the image and the audio, the readers of the novel can only buy it from the text. The sound can be classified into 3 types in the film: speech, music and voice ።

4."Television Drama Introduction" is a drama series that revolves around the same fictional story

## ዋቢ መጽሀፍት


በአዱስ ተስፋ። የፊልም ድርሰት አጻጻፍ ብልሀት። አዱስ አበባ፤ ዛኤዴ ማተሚያ ቤት፤2005።

ብርሀኑ ገብረ/ጻዲቅ ። አጠቃሊይ የአማርኛ ቋንቋ ። አዲስ አበባ ፤ በረከት ማተሚያ ኀ/የተ/የግ/ማ ፤ 2008።

ኤሌያስ ጋሻው ። ስኬታማ የፊልም አሰራር ከመደበኛ ህግጋት ባሻገር ። አዱስ አበባ ፤ ነጭሳር ማተሚያ ድርጅት ፤2007።

ወሰን የለህ ጥላሁን።የፊልም ጥበብ ቅኘት። አዲስአበባ፤ ፋሪኢስትትሬዱንግ፤ 2005።

ዘላለም ተፈሪ ።የፊልም ትወናጥበብ ። አዱስ አበባ ፤ፋሪኢስት ትሬዱንግ ፤ 2010።

ዘሪሁን አስፋው ። የስነጽሁፍ መሰረታዉያን ። አዱስ አበባ ፤ አርቲስት ማተሚያ ቤት 2005።

Bao,Bo.The d/ce b/n novels and films.USA:shaanxi institute of Education,2008

David,self. Television Drama Introduction.london: macmillan company, 1984